# ሞጁል 2

## የአሰልጣኙ መምሪያ

## የመብዛት ተልዕኮ ትምህርት

### ጤናማ ቤተክርስቲያናትን መትከል

multiplication network

*more churches, stronger churches*

ትርጉም፤ ሚልክያስ ለዕላጎ ሽምሱ - 2012

# የብዜት ተልዕኮ
## የቤተክርስቲያን ተከላ ስርአተ ትምህርት ዳሰሳ

| | ሞጁል 1<br>ጤናማ የቤተክርስቲያን ተከላ | ሞጁል 2<br>መልካምን የምስራች ለመናገር መዘጋጀት | ሞጁል 3<br>የእግዚአብሔርን ዕ ቅድ መረዳት | ሞጁል 4<br>መልካሙን ዜና ላሰሙ ማድረስ | ሞጁል 5<br>ሰዎችን ወደ እምነት ማንቀሳቀስ | ሞጁል 6<br>ደቀመዛሙርትን ማሳደግ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማጣኛዎች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያን ተልዕኮአዊ መሰረቶች | የጤናማ ቤተክርስቲያናት ስልታዊ መሰረቶች | ወንጌሉን መኖር | ክርስቲያናዊ እድገት: ክርስቶስ ዕይታችን ማዕከል (ክርስቶስን ማዕከል ማድረግ) |
| ክፍለትምህርት 1 | ጤናማ ቤተክርስቲያን ምንድን ነው? | መንፈሳዊ ካርታ: የጥናት መርሆዎች | እግዚአብሔር ያሳየኝ: የጥናት ውጤትህን ማቅረብ | በእምነት መጽደቅ | የወንጌል እንቅፋት | ታላቁ ተልዕኮ እና ቤተክርስቲያን ተከላ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ተልዕኮ፣ አውድ፣ እና አውዳዊነት | ራዕይ፣ አውድ፣ እና አውዳዊነት | በእግዚአብሔር መጠራትን ማጽናት | ወንጌል | ወንጌል እና ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 2 | ጤናማ የቤተክርስቲያ ተከላ አገልጋይ ምንድን ነው? | ኢየሱስ ይህን አድርጎልኛል! የግል ምስክርነታችሁን ማድርጀት እና ማካፈል | እግዚአብሔር ያሳየኝ: ምስክርነትህን ማካፈልና የጉዞ ጸሎት | የመሪነት መጽሀፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች | የለውጥ ሂደት 1 | የደቀመዝሙርነት ትምህርትን የተሳካ ለማድረግ የሚረዱ መንገዶች |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | መጠራቱ በእግዚአብሔር የተረጋገጠ | ወንጌል | ራዕይ፣ አውድ እና አውዳዊነት | መሪዎችን ማስታጠቅ | ወንጌል | Discipleship |
| ክፍለትምህርት 3 | "የመጨረሻ" አስተሳሰብ: እግዚአብሔር ምን ይፈልጋል? | ትናንሽ ቡድኖችን መምራት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: የእግዚአብሔርን ራዕይ በመንፈስ መረዳት | ወንጌል ስርጭት እና የቤተክርስቲያን ተከላ | የለውጥ ሂደት 2 | Know Your Goal, Know Your People |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል፣ ደቀመዝሙር እና መሪዎችን ማስታጠቅ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል | ወንጌል | ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 4 | የቤተክርስቲያ ተከላ ዙር | ከመጽሐፉ አሳብመውሰድ 2: የእግዚአብሔርን ቃል መመልከት | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: ተልዕኮን መተርጎም | የጥናት ቡድን መመስረት | በቡድን ወንጌልን ማሰራጨት | ከመጽሐፉ አሳብመውሰድ 2: የእግዚአብሔርን ቃል ካለንበት ሁኔታ ጋር ማዛመድ |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ወንጌል እና | ወንጌል | ወንጌል እና ደቀመዝሙር |
| ክፍለትምህርት 5 | አነስተኛ ቡድን ለምን አስፈለገ? | ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህ የጸሎት ቡድን ማንቀሳቀስ | የቤተክርስቲያን ተከላ መሪ ዕቅዱ: እሴትን መተርጎም | ወንጌል እና የማህበረሰቡን አስፈልጎት መድረስ | ልምምድ: የቡድን ልምምድ | ንጽረተ ዓለማትን መረዳት |
| የጤናማ ቤተክርስቲያን ጽንሰ አሳብ | ወንጌል እና ደቀመዝሙር | ወንጌል | ጥርት ያለ ራዕይን ማስተዋወቅ | ግልጋሎት | ወንጌል | በእግዚአብሔር መጠራትን ማጽናት |

# የማብዛት ተልዕኮ

ጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ ሞጁል

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስተሪስ

ብዙ አጥቢያ ያላት/ ጠንካራ ቤተክርስቲያን

2007 ዓ.ም

ይህ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ማኑዋል በAbridged Omega Course እና Multiplication Network Ministries' ጤናማ ቤተክርስቲያን መትከል የተሰኘ የማስተማሪያ መጽሐፍትን በማዋሃድ የተዘጋጀ ነው።

MNM ከ Training Center for Church Planters እና ከ World Ministries ባገኘው ፈቃድ መሰረት ይህን ማስተማሪያ ለቤተክርስቲያን ጥቅም እንዲህ አቅርቦታል።

እናንተም ይህን ማስተማሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መጠበቂያዎች እስከተከተላችሁ ድረስ ይህን መጽሐፍ እንድታባዙና እንድታሰራጩ ማበረታቻችን የሰጠናችሁ ፈቃድ ይሁንልን።

1. ለመጽሐፉ ጸሐፊያን እና ተርጓሚያን ዕውቅና መስጠት
2. መጽሐፉ ላይ ማሻሻያ አድርጋችሁ እንደሆን እርሱን ማሳወቅ
3. ለማሳተሚያ ካወጣችሁት ዋጋ በላይ አለማስከፈል እና
4. ከ አንድ ሺህ ኮፒ በላይ አለማሳተም

ኦሜጋ ኮርስ፦

ተግባራዊ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ማስተማሪያ

| | ለአንድ ቀን ስልጠና የጊዜ ዳዘት እንደ ምሳሌ የቀረበ | |
|---|---|---|
| | የሞጁል አንድ መግቢያ 2 | 2:00 |
| | የትምህርቱ ትኩረት መግለጫ፡- የጤናማ ቤተክርስቲያናት ስነ-መለኮታዊ መሰረቶች | 2:15 |
| | ሪፖርት ማቅረብ | 2:30 |
| ክፍለ ትምህርት አንድ | መንፈሳዊ ካርታ: የጥናት መርሆዎች | 3:00 |
| | ረፍት | 4:00 |
| ክፍለ ትምህርት ሁለት | ኢየሱስ ይህን አድርጎልኛል! የግል ምስክርነታችሁን ማደርጀት እና ማካፈል | 4:15 |
| ክፍለ ትምህርት ሶስት | ትናንሽ ቡድኖችን መምራት | 5:15 |
| | የምሳ ረፍት | 6:15 |
| ክፍለ ትምህርት አራት | ከመጽሐፉ አሳብመውሰድ 2: የእግዚአብሔርን ቃል መመልከት | 7:15 |
| ክፍለ ትምህርት አምስት | ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህ የጸሎት ቡድን ማንቀሳቀስ | 8:15 |
| | የሻይ ረፍት | 3:15 |
| ክፍለ ትምህርት ስድስት | የጸሎት ኮንሰርት: መዝ 95 | 9:30 |
| | መዝጊያ | 10:30 |
| | የቀኑ ጥናት ፍጻሜ | 10:45 |

# መልካሙን የምስራች ለሌሎች ለመንገር መዘጋጀት

## ሞጁል 2

**የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተሳፊዎች ስለሚከተሉት መናገር ይችላሉ፡-**

- ሶስቱ ስነ-መለኮታዊ የቤተክርስቲያን ተከላ ምክንያቶች
- መንፈሳዊ ካርታ እና አስፈላጊነቱ
- አራቱን አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው ቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ግብአቶች እና ጤናማ ሂደት
- ከመጽሐፉ ሃሳብ በመውሰድ የማጥናት ዘዴ ላይ ምልከታ ማድረግ ምን ማለት ነው
- ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች እንዴት አድርገው ለአገልግሎታቸው የጸሎት ህብረት ማቋቋም እንደሚችሉ የሚማሩበት ተግባራዊ ልምምድ
- ጤናማ ቤተክርስቲያን የመትከል መሰረታዊ ሂደት

## የሞጁል 2 መግቢያ

### የአሰልጣኙ ትውውቅ ጸሎት (2 ደቂቃ)

- ተሳታፊዎችን ሞቅ ባለ፣ ፍቅር በተሞላ እና በሚያነቃቃ ሁኔታ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትህን አቅርብ
- ከዚያም በጸሎት የቀኑን ትምህርት ለእግዚአብሔር ክብር ይሆን ዘንድ አሳልፈህ ስጥ

### ወደ አዲሱ ተግባራዊ ልምምድ ተሻገር (5 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ተሳታፊዎች በአንድ መስመር እንዲሰለፉ አድርግ
- በሰልፉ መጀመሪያ ላለው ሰው "ከዋንዛ የተሰራው ጠረጴዛ ወደንጠጅ ሲቀባ አያምርም" ብለህ በጆሮው ቀስ ብለህ ንገር
- ከዚያም እርሱ ቀጥሎ ላለው ይህንኑ ይናገር እንዲህ እያለ በሰልፉ መጨረሻ እስከተሰለፈው ሰው ድረስ ይናገር
- ከዚያም የመጨረሻው ሰው የሰማውን እንዲናገር ካደረክ በኋላ ለመጀመሪያው ሰው የተናገርከውን መልዕክት ለተሳታፊዎች ተናገር፡፡ በተለምዶ በእንዲህ ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመሪያ በተነገረው እና መጨረሻ በሚነገረው መልዕክት መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይኖራል፡፡ የሳቅ ጊዜ እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡

እንዲህ በል፡- "በዚህ ሞጁል እንዴት አድርገን መልካሙን የምስራች ጥርት ባለና የሚሰሙን ሊረዱን በሚችሉ መንገድ ማቅረብ እንደምንችል እንማራለን፡፡"

### የመልክአ ምድር ካርታዎች ጠቀሜታ (8 ደቂቃ)

**ለአሰልጣኙ የሚሆን ማሳሰቢያ፡-** የዚህ ተግባራዊ ልምምድ ዋናው አላማ መልክአምድርን የምንተዋወቅባቸው ካርታዎች ምን አይነት መረጃ እንደሚሰጡን ተሳታፊዎች ማሰብ እንዲጀምሩ ነው፡፡

- ጠቅላላውን ተሳታፊ ከ4-5 ሰው በያዙ ትናንሽ ቡድኖች ከፋፍላቸው፤ ከዚያም በያዙት ካርታ ላይ ያሉ ዋና ዋና ነገሮችን እንዲመዘግቡ 2 ደቂቃ ስጣቸው
- እየንዳንዱ ቡድን በካርታው ላይ የተመለከታቸውን ዋና ነገሮች ሶስቱን እንዲናገሩ እድል ስጣቸው
- ከተሳታፊዎች ሁለት ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ምረጥና ካርታው ለምን እንደሚጠቅም (ለምሳሌ፤ ከአንድ ስፍራ ወደሌላ ስፍራ እንደውሃ ያሉ ግብአቶች መገኛ ስፍራቸውን ለማወቅ እና ለመሳሰሉት) በመጠየቅ አሳባቸውን እንዲሰጡ አድርግ፡፡
- ለተሳታፊው ሁሉ እንዲህ በል "ዛሬ የነገሮችን መገኛ ስፍራ ከካርታ ላይ ማንበብ እና በካርታ ላይ ማስፈር ለቤተክርስቲያን ተክላ እንዴት እንደሚጠቅም እንመለከታለን"

# የቤተክርስቲያን ተከላ ስነመለኮታዊ መሰረቶች (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** እንዲህ በል "ዛሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ አራት የተለያዩ የምንባብ ክፍሎችን በማንሳት እንዴት የእግዚአብሔር ተግባር ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ስራ ላይ ምን አይነት ሚና እንደሚጫወት እና እንዴትስ እንደቤተክርስቲያን አገልጋይ እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መስራት እንደምትችሉ እንማራለን"

**መግቢያ**

- እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስትስ አለሙን ሁሉ ከራሱ ጋር ያስታርቃል፡፡
- መንፈስቅዱስ ቤተክርስቲያን በተገለጠው ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ አለምን ሳልጠቀለለው የእግዚአብሔር መንግስት አይነተኛ መገለጫ ትሆን ዘንድ በኃይል ያስታጥቃታል፡፡
- እግዚአብሔር የእርሱን የመዋጀት ፍቅር በአዲስ መንገድ እንዴት በእምነት፣ተስፋና ፍቅር ማህበረሰብን መፍጠር እንደሚቻል ለአለም ለማሳየት ቤተክርስቲያንን "ሰርቶ ማሳያ" አድርጎ ይጠቀምባታል፡፡
- እኛ እና እንደክርስቲያን ያለን ንጽረተ አለም፤ በፍቅር እና በጸጋ የተሞላው እግዚአብሔር አለምን በልጁ በክርስቶስ ካደስ (አዲስ ካደረገ) በኂላ የእርሱ የሆኑት ከእርሱ ጋር አብርስራተኛ ይሆኑ ዘንድ እየጠራ፣ በቅዱስ ቃሉ ላይ በመመስረት እና በመንፈስ በመመራት፤ የእርሱን ምጽአት ብርሃን በማንጸባረቅ፣ አለምን በክርስቶስ መጠቅለል ነው፡፡

**የአሰልጣኙ መምሪያ:-** ጠቅላላውን ተሳታፊ በአራት ቡድን ከፈልና ለእያንዳንዱ ቡድን ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል ስጣቸው፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ቡድን ጥያቄዎችን በራሱ እንዲመልስ፤ በመጨረሻም ለጠቅላላው ተሳታፊ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

እንዲህ በል "እያንዳንዱ ቡድን የደረሰውን ጥያቄ በተወካዩ አማካይነት ለሁሉም ተሳታፊ በንባብ በማሰማት አራቱ ጥያቄዎች እንዴት እንደሚገናኙ ተወያዩ"

**የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሎች:-**

1. ሐዋ 3፡17-21

2. ኤፌ 1፡7-10

3. ቆላ 1፡16-20

4. ሮሜ 8፡19-23

**የውይይት ጥያቄዎች፡-**

1. በምንባብ ክፍሉ መሰረት የእግዚአብሔር ተግባር ምንድን ነው?

2. ይህ ተግባር ስለምን አስፈላጊ ሆነ?

3. ይህ ተግባር የቤተክርስቲያን ተከላ ላይ ምን አይነት ሚና ይኖረዋል?

4. በእግዚአብሔር የመዋጀት ተግባር ውስጥ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ድርሻና ለዚህ ተግባር የሚያዋጣው ግብአት ምንድን?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "ፍጥረት ሁሉ እያየ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሰራተኛ መሆን እንዴት ያለ አስደሳች እውነት ነው፤ እንዴትስ መታደል ነው! የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ወንድና ሴት እንዲሁም ወጣትና አዛውንትን በአንድነት በማምጣት አንድን አዲስ የአማኞችን ማህበረሰብ በመፍጠር፤ የእምነት፣ ተስፋ እና ፍቅር መገለጫ መሆን የሚችል የማህበረሰቡን አውድ የጠበቀ ይዘት ለመፍጠር የሚሰራ ነው፡፡"

ሁለት ወይም ሶስት ተሳታፊዎችን እስካሁን በተወያያችሁባቸው በምስጋና እንዲያጠናቅቁ እና ቀጣዩንም የጥናት ጊዜ ለጌታ ክብር በጸሎት እንዲያስረክቡ አድርግ፡፡

**ሪፖርት ማድረግ (30 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- እንዲህ በል "በሞጁል 1 ጥናታችን "የመጨረሻ" እቅዳችሁን እንድታጠናቁ ተጠይቃችሁ ነበር፤ በዚህ ክፍል ደግሞ ጥናት ለማድረግ የምትወስዱትን ተነሳሽነት ለማገዝ የሚረዳችሁ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል፡፡ ስለ ጥናትና ምርምሩ በጥልቀት ከማንሳታችን በፊት በዚህ ክፍለትምህርት የተሰጣችሁን የቤት ስራ ሪፖርት አድርጉ፡፡" (15 ደቂቃ)
- ጠቅላላውን ተሳታፊ ለሶስት በመክፈል እያንዳንዱ ተሳታፊ ስለተሰጠው የቤትስራ ሪፖርት እንዲያደርግ 5 ደቂቃ ስጥ፡፡
- እያንዳዱ ቡድን በዙር ተግባራዊ እንቅስቃሴውን እንዲመለከት እድል ስጥ
- ምናልባት የቤት ስራቸውን ያልሰሩ ተሳታፊዎች ካሉ በእረፍት ሰዐት ሊታናገራቸው እደምትፈልግ በመንገር ቀጠሮ ያዝ፤ ከዚያም ቀጣዩ ክፍለ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት እንዲያጠናቅቁ አሳስባቸው፡፡
- ጊዜ የሚበቃ ከሆነ ሶስት ሰዎች ግንኙነታቸውን ለጠቅላላው ተሳታፊ እንዲያቀርቡ እድል ስጥ፡፡
- እንደገና ጊዜ የሚበቃ ከሆነ ከመጽሐፉ መልዕክት የመውሰድ የጥናት ስልት እቅድን ክንውን ለመቆጣጠር ጊዜ ስጥ፡፡

## ለሞጁል 2 የሚሆኑ የትግበራ እቅዶች

## (ከሞጁል 1 ክፍለ ትምህርት 3)

1. ቤተክርስቲያን ለመትከል ያቀዳችሁበትን ስፍራ ካርታ በማዘጋጀት በዚህ ስፍራ የሚገኙ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናትንሊኖሩቸው ከሚችል የቦታ ስፋት ግምት ጋር በማቅረብ፤ በዚያ ሊኖር የሚችለውን የህዝብ ብዛት በማወቅ" ቤተክርስቲያን የምትተከልበትን ከተማ እና ልዩ ስፍራ መወሰን፡፡

አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎች እንዳስቀመጡት ቤተክርስቲያን በበቂ ሁኔታ አለ ለማለት ወይንም ቤተክርስቲያን ተከላ በአንድ አካባቢ "ፍላጎትን አሟልቷል" ለማለት አንድ ቤተክርስቲያን ለአንድ

ሺህ ሰው መድረስ ሲችል ብቻ ነው፡፡ስለአንድ ሺህ ሰው አንድ ቤተክርስቲያን በሚለው ከተስማማን እናንተ ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰባችሁት ከተማና ልዩ ስፍራ ምን ያህል ቤተክርስቲያናት መትከል ይገባቸዋል?

2. ስለቤተክርስቲያን ተከላ ስታስብ እቅድህን ሁሉ ለማድረግ ጸሎትን፣ አንድነት እና ፍቅርን፣ ራእይን፣ ወንጌል ስርጭትን እና የቤተክርስቲያን ተከላን አካቶ ማሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ የመነሻ የሚሆንን አሳብ ጻፍና ለአማካሪና ደጋፊህ አሳብህን አካፍል፡፡

3. ስለ ቅርብ አካባቢህ፣ መንደርህ፣ ከተማ እና ክልል፣ ወይንም አገር በማሰብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይህን ከግምት ውስጥ አስገባ፡-

- እግዚአብሔር ለ____________________ (ቤተክርስቲያን መትከል ያሰብከበትን ከተማ፣ መንደር፣ ወይንም የቅርብ አካባቢ ስም አስገባ) ምን ይፈልጋል፡፡
- በዚህ አካባቢ እንዲሆኑ የምትፈልጋቸውን ሶስት "የመጨረሻ" ውጤቶች ጻፍ፡፡

## ለሞጁል 2 የሚሆን የትግበራ እቅድ

### (ከሞጁስ 1፤ ክፍስ ትምህርት 6)

ቀጣዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክፍል በዚህ የአጠናን ዘዴ ተጠቀመን ምልከታን ለማከናወን ከአንድ አንቀጽ ያልበለጠ ክፍል ውሰዱ፡፡ ለመረጣችሁት አንድ አንቀጽ በትንሹ አንድ ሰአት ወስዳችሁ በመንፈሳችሁ እግዚአብሔር የውስጥ አይናችሁ እንዲበራ እና በዚህ ክፍል የተገለጠውን እውነት ማወቅ ትችሉ ዘንድ እየጸለያችሁ ምልከታችሁን አካሂዱ፡፡ ከዚያ ምልከታችሁን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡ ምን ተማራችሁ? ከዚህ ክፍል የተማራችሁትን በቀጣይ ክፍስ ትምህርት አብረዋችሁ ለሚሰለጥኑ ተሳታፊዎች ለማቅረብ ተዘጋጁ፡፡

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡- (15 ደቂቃ)**

- ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው የሚገኘውን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ ሀ.ለ.መ ቅጽን እንዲመለከቱ ማድረግ፡- ወርሃዊ ሪፖርት በማንሳት በዚህ ኮርስ የሚጠበቀውን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አብራሩ፡፡
- እንዴት በዚህ ቅጽ ላይ መረጃን እንደሚሞሉ አስረዳ
- እንዴት አድርገው አንዱ ቡድን ለሌላው ከሞጁል 1 እንስከ 12 ሪፖርቱን እንደሚያቀርብ አስረዳ፡፡

# መንፈሳዊ ካርታን ማዘጋጀት፡

# የምርምር ጽሑፍ መርሀ (60 ደቂቃ)

## የመንፈሳዊ ካርታ ትርጉም (30 ደቂቃ)

### I. መንፈሳዊ ካርታ ምንድን ነው?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** እንዲህ በል "በቤተክርስቲያን ተከላ ሂደት ውስጥ አንዱ የሚከወን ጉዳይ ለእግዚአብሔር መንግስት ጥቅም የሚውል መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በተመሳሳይ የወንጌል ተልዕኮ አገልጋዮች ይህን ሂደት መንፈሳዊ ካርታ ብለው ይጠሩታል በዚህ ክፍለትምህርት የምርምር ጽሑፍ የሚለውን እና መንፈሳዊ ካርታ የሚሉትን ቃላት እንጠቀማለን ሁለቱም ቃላት ስለሁለቱም መሰረታዊ የጥናት አቀጣጫዎች ማብራሪያ የሚሆን መረጃን የምንሰበስብበትን ሂደት ለማሳየት የሚገባ ነው፡፡"

ተሳታፊዎች ከዚህ በታች ሳለው አርፍተ ነገር የጎደሉትን ቃላት በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ እንዲሞሉ ጠቁማቸው፡፡

መንፈሳዊ ካርታ መስራት ማለት ለእግዚአብሔር መንግስት መስፋት ዓላማ መረጃን መሰብሰብ ሲሆን ትኩረቱም፡-

1. የመኸሩ መስክ፡- ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰብክበት ስፍራ እና በዚያ የሚኖር ህዝብ፡፡

2. የመኸሩ ሰራተኞች፡- የቤተክርስቲያን ተከላውን ለመደገፍ የሚሰሩ ሰዎች፣ ቤተክርስቲያናት፣ ሌሎች ድርጅቶች፣ እና ሌሎች ቡድኖች፡፡

### II. ስመንፈሳዊ ካርታ መስራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቶች

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ጠቅላላውን ተሳታፊ (ከተቻለ ለ6) ቡድን መክፈል
- ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ ለቡድኑ እንዲበቃ አድርጎ ማካፈል፤ ከዚያም በዚህ ምንባብ ውስጥ ምን አይነት መረጃዎች እንደ ሪፖርት እንደሰፈረ እና ለምን እነዚህን መረጃዎች በዚህ ውስጥ እንደ ሪፖርት ማካተት ጠቀሜታው ምንድን ነው፡፡
- ጥቂት ጊዜ ወስደህ በዚህ የተካተቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሎች ምን አይነት መረጃ እንደያዙ እና ቤተክርስቲያን በመተከሉ ረገድ እንዴት ልንጠቀምባቸው እንደምንችል ደረጃ ዘንድ የውይይት ጊዜ እንዲኖራቸው አድርግ፡፡

1. ዘኍ 13፡1-4

**የተጠቀሰው የመረጃ አይነት፡-** ምድሪቱን ይሰልሉ ዘንድ ሰላዮች ተላኩ

**አስፈላጊነት፡-** ስለምድሪቱ ነዋሪዎች የአኗኗር አውድ ቀድሞ ለማወቅ፡፡

2. ነህ 1፡3-4፤ 2፡1-6

**የተጠቀሰው መረጃ አይነት፡-** ነህሚያ ቅጥሩን መገንባት ከመጀመሩ አስቀድሞ ስለ ኢየሩሳሌም ሁኔታ እና ደህን የቅጥር ስራ አብረው የሚሰሩትን ሰዎች የሞራል ሁኔታ ቀድሞ አጥንቶ ነበር፡፡

**አስፈላጊነት፡-** ቅጥሩን የመስራት አስፈላጊነት እና ለዚህ የሚሆን ግብአት ይዘትን ለመረዳት፡፡

3. ማቴ 9፡35 - 10፡1

**የተጠቀሰው መረጃ አይነት፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ከእነርሱ ጋር ይሰሩ ዘንድ ከመላኩ በፊት የማህበረሰቡን ፍላጎት ቀድሞ በስፍራው በመገኘት አጥንቶ ነበር፡፡

**አስፈላጊነት፡-** ሰዎችን እና ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ

4. ዮሐ 4፡35

**የጠቀሰው የመረጃ አይነት፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ የነፍሳትን መኸር "እንዲመለከቱ" ወይንም "እንዲመረምሩ"(የግሪኩ ቃል ትርጓሜ) አዘዛቸው፡፡

**አስፈላጊነት፡-** እግዚአብሔር እያቀናጀ ያለውን መልካም አጋጣሚ በጥንቃቄ እንዲመለከቱ

5. ሐዋ 1፡8

**የተጠቀሰው የመረጃ አይነት፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ ወንጌልን ለአለም ለማድረስ ቁልፍ ስፍራ (ስልታዊ ጠቀሜታ) ካለው (የአይሁዳዊያን ዓለም ማዕከል ከሆነው ኢየሩሳሌም) ጀምረው እየሰፋ በሚሄድ የከባቢ ደዘት (ይሁዳ፣ ሰማሪያ እና የምድር ዳርቻ) እንዲያደርሱ አዘዛቸው፡፡

**አስፈላጊነት፡-** እግዚአብሔር እየሰራ ያለውን በንቃት እንዲመለከቱ እና አንዲያደንቁ

6. ሐዋ 2፡41፣ 47፤ 4፡4፤ 5፡14

**የተጠቀሰው የመረጃ አይነት፡-** ስለሰው ብዛት የተደረገ ሪፖርት

**አስፈላጊነት፡-** እግዚአብሔር እየሰራ ያለውን በንቃት እንዲመለከቱ እና አንዲያደንቁ

## III. ለምንድን ነው የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩ መንፈሰዊ ካርታ መስራት የሚያስፈልገው?

- በወንጌል ልንደርሳቸው ላሰብናቸው ሰዎች ርህራሄ እንዲሰማን የሚቀሰቅስ ስለሆነ
- መረጃው ለጸሎት ስለሚያነሳሳ እና በምን ርዕስ ላይ መጸለይ እንደሚገባ ስለሚገልጥ
- መረጃው ቤተክርስቲያን የመትከል ራዕይን ስለሚያነሳሳ
- መረጃው የመኸሩን ሰራተኞች የበለጠ ውጤታማ ስለሚያደርግ

## IV. መቼ ነው መንፈሳዊ ካርታ የሚከሰተው?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ይህ ክፍል ትምህርት በሞጁል 1 የተገለጠውን የቤተክርስቲያን ተከላ ዙርን ደግመን እንድንመለከት የተዘጋጀ ነው። ጊዜ የሚፈቅድ ከሆነ መልሶ ይህን ክፍል ከሞጁል 1 መመልከት አስፈላጊ ነው።

በእርግጥ መንፈሳዊ ካርታ በመጀመሪያ የሚከሰተው በክፍል (Phase) 1- በጸሎት፤ በተጨማሪም ለክፍል (Phase) 4- ለመሰባሰብ ለሚለው (Phase) ጠቃሚ ሲሆን ይችላል። በዚህ ሁኔታ መንፈሳዊ ካርታ አዲስ የምንተክለው ቤተክርስቲያን ውጤታማ መሆን አስመሆኑን የምንለካበት መሳሪያ ሆኖ ያገለግለናል። ከዚህም በተጨማሪ መንፈሰዊ ካርታ ለክፍል (Phase) 5 ማለትም የመባዛት (Phase) ቤተክርስቲያኒቱ ያላትን ሚና "ከፍ አድርጋ" እንድትመለከትና የክርስቶስ አካልን ሰፊ ስራ በጥንቃቄ እንድታስተውል ይረዳታል።

## V. መንፈሳዊ ካርታ ከየት ነው መከሰት የሚገባው?

**የአሰልጣኙ ዝግጅት፡-** ለተሳታፊዎች ምሳሌዎችን አዘጋጅ። ልትደርሱት ያቀዳችሁትን ስፍራ ካርታ ሳሉና በምትሰጡት ምሳሌ ውስጥ በእቅድ ለስያዛችሁት ስፍራ መረጃዎችን አስገቡ። ካርታውን እንደየአስፈላጊነቱ ለተሳታፊዎቹ ልናስተላልፈው የምንፈልገውን ሐሳብ እንዲይዙ አድርጎ በማስተካከል ቤተክርስቲያናት የት እንደሚገኙ እና ምን አይነት ቤተክርስቲያናት እንደሆኑ እንዲሁም ሌሎች ለስራችን አስፈላጊ የሆኑ አቅራቢያ አካባቢዎችን ማሳየት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡- የኃይማኖት ማእከላት፣ የፖለቲካ ማዕከላት፣ የገበያ ስፍራዎች፣ ታሪካዊ ስፈራዎች ወዘተ...

መንፈሳዊ ካርታ  እንደ (የቅርብ አካባቢ፣ መንደር፣ ከተማ) ያሉ ልዩ ስፍራዎች እና ሰፋያለ መልክአምድራዊ ይዘት ያላቸው እንደ (አገር፣ ዞን እና ክልል) ለቤተክርስቲያን ተከላ ትመርጡ እንደሆን እነዚህን የሚያካትት መሆን ይገባዋል።

## VI. እንዴት ነው መንፈሳዊ ካርታ የሚሰራው

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- እንዲህ በል "እናንተ የመረጣችሁትን ቦታ ወይንም አካባቢ በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ የምታገኙበት የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፤ የተወሰኑትን በመማሪያ ደብተራችሁ እንድትመዘግቡ ይሁን"

1. የመስክ <u>ምልከታ</u>

2. <u>ቃለመጠይቅ</u>

3. መጠይቅ እና <u>ዳሰሳ</u>

4. እናንተ ስለመረጣችሁት አካባቢ <u>የመንግስት</u> መረጃ

5. ሌሎች የህትመት ሚዲያዎች (እንደ መጽሐፍት፣ ጆርናሎችና ወ.ዘ.ተ)፣ <u>ምስል</u> እና <u>የድምጽ</u> መረጃዎች እናንተ ስለመረጣችሁት አካባቢ ምን ይላሉ የሚለውን ማወቅ።

## VII. መንፈሳዊ ካርታን መጠቀም መጀመር

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ተሳታፊዎች ለሁለት ወይንም ለሶስት ሆነው ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ አድርጉ
- ጥቂት ጊዜ መውሰድ ከቻላችሁ ተሳታፊዎች መልሳቸውን ለጠቅላላ ተሳታፊዎች እንዲያቀርቡ እድል ስጡ።

1. አገልግሎታችሁን ልትጀምሩ ስላሰባችሁበት ቦታ ጥናት ማድረግ ምን አይነት ጥቅም ይሰጣል?

______________________________

______________________________

______________________________

2. ጥናትና ምርምር የቤተክርስቲያን ተከላ ጥረትን እንዴት ውጤታማ ያደርጋል?

3. ባሰብከው ስፍራ ላይ የምታከናውነውን የቤተክርስቲያን ተከላ ጥረትህን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አምስት ወይንም ስድስት አይነት መረጃዎች ምን ምን ናቸው?

4. ጥናትና ምርምርህ አገልግሎትህን ልትከውን ስላሰብከው ስፍራ ምን አይነት ውጤት የሚያስገኝልህ ይመስልሃል? በመኸር መስክህ ያሉ ሰዎች ወንጌልን ለመስማት ዝግጁ ናቸው? አንተ ካደረካቸው ምልከታዎች ሰዎች ለወንጌል ልባቸው ክፍት ወይንም ዝግ (ተቃዋሚ) መሆናቸውን ምን አይነት ጥቆማ ሰጥትሃል?

5. ማነው መረጃን የሚሰበስበው? ካሰለጠንካቸው በኋላ ጥናት እና ምርምርን በመገንባት መከወን የሚችሉ ተሳታፊዎችን ለይተህ ታውቃለህ፤ እነማን ናቸው?

6. ማን ነው የጥናቱን ግኝት መረጃ አጠቃሎ የሚያቀርበው? መረጃውን አጠቃሎ የሚያቀርበው ግለሰብ ቤተክርስቲያን ልንተክልበት ያሰብነው አካባቢ ላሉ ሰዎች ርህራሄ እንዲሰማን ማድረግ የሚችሉ እና እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ምን ሲሰራ እንዳሰበ በመግለጥ በራስ መተማመንን በአገልጋዮች ላይ የመፍጠር ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡

## ለሞጁል 3 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡- መንፈሳዊ ካርታን በመጠቀም ልትደርሱት ያቀዳችሁትን ስፍራ/አካባቢ መረዳት (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች የቀረበውን የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዩን መምሪያ በመዳሰስና ስድስቱን የምርምር ደረጃ ሂደቶች ከተሳታፊዎች ጋር በመሆን በመዳሰስ የዚህን ክፍል ትምህርት የቤት ስራ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ወደ ሶስተኛው ሞጁል ከመመለሳችን በፊት፣ ከዚህ በታች የቀረቡትን ስድስቱን የጥናትና ምርምር መንገዶች በመከተል ለአገልግሎት የመረጥከውን ስፍራ አጥና። ከዚህ በታች የቀረበውን ናሙና እንደየአስፈላጊነቱ ለጥናታችሁ መጠቀም ትችላላችሁ።

የዚህ የቤት ስራ አላማ ለቤተክርስቲያን ተከላ ውጤታማ የሆነ የጥናትና ምርምር መሳሪያን በተግባር እንድትለማመዱ ነው። እያንዳንዱን የቤት ስራ ክፍል ለመስራት መሞከር አለባችሁ፤ አንዳንዶቹን ተግባራት ከሌሎች በጣም ቀለል ብላ ታገኟቸዋላችሁ በእያንዳንዱ የቤትስራችሁ ይቀለልም ይክበድም እግዚአብሔር ለአገልግሎት ስለጠራችሁ ስፍራ፤ በእያንዳንዱ የትግበራ ጥረታችሁ የሚያስተምራችሁ አንዳች ነገር አለው።

ይህን የቤት ስራ ራሳችሁ በራሳችሁ መስራት አትገደዱም፤ ከሌሎች ጋር መስራት ይቻላል። እንደውም የሚቻል ከሆነ ሌሎችን ማሳተፍ የሚመከር ነው። በመጨረሻም የምርምር ግኝትህን ለአሰልጣኝህ፣ በምክርና ድጋፍ ለሚያገለግልህ እና ለሌሎችም ለማቅረብ ዝግጁ ሁን።

እግዚአብሔር ይህን ጥናት ተጠቅሞ ልታገለግል ያሰብካቸውን ማህበረሰቦች በርህራሄ የምትምለከትበት እና ስለእነርሱ ደግሞ ጠለቅ ያለ ዕውቀት እንዲኖርህ እንዲያደርግ፤ ይህን ጥናት ተጠቅሞ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎታችሁን የት እና እንዴት መጀመር እንዳለባችሁ እንዲያመለክታችሁ እንዲናገራችሁ ጸልዩ።

## ባለ ስድስት ደረጃ የጥናትና ምርምር ሂደቶች (15 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ተሳታፊዎች ስድስቱን የጥናትና ምርምር ደረጃዎች በሚሞሉበት ሂደት እንዴት አድርገው በሚቀጥለው ሞጁል ሪፖርት ማቅረብ እንደሚችሉ ምራቸው፡፡ በዚህ ሞጁል መጨረሻ ስለሰፈረው የመጠይቅ ናሙና ለተሳታፊዎች ጥቆማ ስጥ፡፡

ደረጃ 1፡- ለአገልግሎት የመረጥከውን ስፍራ ወስን

ለአገልግሎት የመረጣችሁትን መንደር፣ ከተማ ወይንም ክልል የሚገልጥ ካርታ አዘጋጅ፤ ከተቻለ ሁሉንም መረጃ ያጠቃለለ ማለትም የህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎችን፣ የጎዳና ስሞች እና የትራንስፖርት መነሻ እና መድረሻ የሚያሳይ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ከዚያም በዚህ ካርታ ላይ ለአገልግሎት የመረጥከውን ስፍራ አክብብ፡፡ ታዲያ ይህ ያከበብከው ስፍራ የእግዚአብሔርን ስም ይታወቅ ዘንድ ቤተክርስቲያን ትተከል ዘንድ እግዚአብሔር የጠራህ ስፍራ ነው፡፡

ደረጃ 2፡- በዚህ መኸር ስራ ሊሳተፉ የሚችሉ ሰራተኞች መረጃ መሰብሰብ

ከላይ ለመተርጎም እንደሞከርነው የመኸሩ ሰራተኞች ማለት እግዚአብሔር ለአገልግሎት ለተመረጠው ስፍራ ያዘጋጀው ግብአት ነው፡፡ የሚከተሉትን በማጥናት እግዚአብሔር አንተን ለጠራበት ስፍራ እግዚአብሔር ያዘጋጀኸውን ግብአት ምን እንደሆነ ተመልከት፡-

1. በዚያ አካባቢ ቀደም ብለው የተተከሉ ቤተክርስቲያናት

    ሀ. በዚህ ስፍራ የሚገኙ ቤተክርስቲያናት ሁሉ የት እንዳሉ በካርታህ ላይ ምልክት አድርግ፤ በተጨማሪም ምን አይነት ቤተ እምነቶች እንደሆኑ አመልከት

    ለ. የሚቻል ከሆነ በእነዚህ ቤተክርስቲያናት የሚገኙ አባላት ቁጥርን መዝግበህ ያዝ

    መ. እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን መቼ እንደተተከለ ወይንም መቼ እንደገና እንደተጀመረ አመልከት

ሰ. እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ምን አይነት የማህበረሰብ ክፍልን እየደረሰ ይገኛል፡፡ ምን ያህልስ ጥረታቸው የተሳካ ነው?

ረ. በዚህ ስፍራ የሚገኙ ክርስቲያን ማህበረሰብ በመደበኛ ጊዜ ወስነው ለጠፉት ነፍሳት ወይንም በተለይ ለሚያገለግሉ ወንጌላውያን ይጸልያሉ?

2. የወንጌል ተልዕኮ እና ቤተክርስቲያናትን ደጋፊ አገልግሎት ቡድን

ሀ. ለአገልግሎት በተመረጠው ስፍራ የሚገኙ የወንጌል ተልዕኮ እና ቤተክርስቲያናትን ደጋፊ ቡድኖች ካሉ ሁሉንም መመዝገብ አስፈላጊ ነው፡፡

ለ. እያንዳንዱ በአካባቢው ያለ ሚኒስትሪ ምን አይነት የአገልግሎት ዘርፍ (ለምሳሌ፡- ስነጽሑፍ፣ የእስር ቤት አገልግሎት፣ የወጣቶችና ወ.ዘ.ተ) እንዳላቸው ዘርዝር

መ. ከእናንተ ወይንም ከሌሎች ጋር በወንጌል ስርጭት እና የቤተክርስቲያን ተከላ ጥረታችሁ ላይ ተሳታፊ ስለመሆን ፍላጎት አላቸው?

3. የክርስትና እምነት ታሪክ

ሀ. አገልግሎታችሁን መጀመር ያሰባችሁበት ስፍራ ወንጌል መቼና እንዴት ደረሰ? ማህበረሰቡ በፈቃዱ ነው አማኝ የሆነው ወይንስ በግድ ተጭኖባቸው?

ለ. በዚህ ስፍራ ያሉ ቤተእምነቶች እንዴት እንደመጡ አስረዱ፡፡

መ. በመረጣችሁት ስፍራ ተጽዕኖአቸው ከፍ ያለ ሌሎች ኃይማኖቶች አሉ? አሁን ባለህበት አካባቢ ምን አይነት ኃይማኖቶች/የስህተት አስተማሪዎች አሉ? ተከታዮችን በማፍራት ረገድስ ምን ያህል እየተሳካላቸው ይገኛል?

ሰ. ከላይ ያነሳነው ታሪክ ለእናንተ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ላይ ምን አይነት ሚና

ይጫወታል?

**ደረጃ 3፡- ስለመኸሩ <u>መስክ</u> መረጃን መሰብሰብ**

የመኸር መስክ ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰባችሁበት ስፍራን እና በዚያ የሚኖረና አገልግሎታችሁን ለትመሰርቱባቸው ያሰባችሁበት የማህበረሰብ ክፍሎችን ወይንም ጠቅላላውን ህዝቡን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ከዚህ በታች ያለው ተግባራዊ ልምምድ ስለመኸሩ መስክ ወይንም ቤተክርስቲያን ለመትከል ስለመረጣችሁት ስፍራና ህዝብ ትምህርት ትወስዱ ዘንድ የሚረዳ ነው፡፡

1. <u>የህዝብ ብዛትን</u> የተመለከተ መረጃ

ሀ. ጠቅላላው የህዝብ ብዛት

ለ. ከጠቅላላው ህዝብ ቁጥር ውስጥ የወንድ፣ የሴት፣ የወጣት፣ እና የልጆች ብዛት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ፡፡

መ. በስራ የተሰማራው የማህበረሰብ ክፍል…እንዲሁም የሙያ ዘርፋቸው እና የገቢ መጠናቸው

ሠ. በጡረታ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ አዛውንቶች እና ከተለያየ የአካል ጉዳት ጋር

የሚኖሩ ህዝቦች ቁጥር

ሸ. በመረጣችሁት አካባቢ የሚኖሩ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ጎሳዎች፤ ምን አይነት ቋንቋ ነው የሚናገሩት?

2. <u>መልክአምድራዊ</u> መረጃ

የቤተክርስቲያን ተከላ እቅድ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳርፉ ጉዳዮች አንዱ የመልክአምድራዊ መገኛ ሲሆን ሰዎች የት እንደሚኖሩ እና ከየትኛው የማህበረሰብ ክፍል ጋር እንደሚዛመዱ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ሁአንድ የባቡር መስመር ቡስቱ አቅጣጫ የሚኖሩ የአንድ መንደር ሰዎች በአንዱ አቅጣጫ ያሉ ሃብታሞች በሌላው አቅጣጫ ደግሞ ያሉ ድሆች ሲሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎች ከአንዱ

አቀጣጫ ወደሌላኛው አቅጣጫ መሻገር የሚፈልጉ አይመስሉም። የባቡር መስመሯ በማህበረሰቡ መካከል የቆመ ግድግዳ ሲሆን በአንዱ አቅጣጫ ያሉት ተሻግረው በሌላኛው አቅጣጫ ያለ ቤተክርስቲያን ማገልገል አይፈልጉም። ሌላ ምሳሌ እናንሳ፤ አንድ በጣም በሚያምሩ ተራሮች የተከበበ ሲሆን በዚያ ከተማ የሚኖሩ አማኞች እሁድ እሁድ ከከተማ ወጣብለው ዘና ማለት ስለሚፈልጉ የእሁድ ፕሮግራሞችን ሳለመካፈል እንደምክንያት ይሆንባቸዋል።

ሀ. ምን አይነት ነገር ነው ክልሉን የከፈለው/ድንበር የሆነው (ወንዞች፣ የባቡር መስመር፣ መንገዶች ወ.ዘ.ተ…)

ይህ የወሰን አመላካች በሰዎች እንቅስቃሴ፣ ህብረት ወ.ዘ.ተ ላይ ምን አይነት

ተጽዕኖ አሳድሯል?

ለ. ከተማው በተራራ የተከበበ ነው? ወጣ ብሎ ለመዝናናት የሚሆኑስ እንደ ሐይቅ፣ የባህር ዳርቻ፣ ፓርኮች፣ ወይንም እንዲህ ያሉ ሌሎች መዝናኛዎች አሉ?

መ. ልታገለግልበት የመረጥከው ስፍራ ከተማ ከሆነ የመኖሪያና የኢንዱስተሪ አካባቢዎችን

ከካርታህ ላይ ተመልከት። በዚህ ስፍራ የተለየ የገበያ ስፍራ አለ? ሰዎች በእነዚህ

ኢንዱስተሪ አካባቢዎች ይኖራሉ ወይስ ረጅም መንገድ ተጉዘው ነው የሚመጡት? የትነው ሰው የሚሰበሰበው? ከዚህ በኋላ ሰዎች ለትራነስፖርት የሚጠቀሙበት ዋና መጓጓዣ

ምንድን ነው? አብዛኛው ሰው በምንድን ነው የሚጓዘው፤ በመኪና፣ በባስ፣ በእግር?

ሰ. የት ነው ማህበረሰቡ ለመዝናናት የሚሄደው? በከተማ ውስጥ ባለ ፓርክ ነው የሚዝናኑት?

3. <u>ማህበረሰባዊ</u> እና <u>ባህላዊ</u> መረጃ

የሰዎችን አጀርተ አለምና ፍላጎት በሚገባ በማጥናት ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መንገድ እንዲያውቁ የምናደርግ መገለጥ ይኖረናል። ለሰዎች ለመማር ተመራጭ

የሚባለው መንገድ ጥያቄ መጠየቅ እና የሰዎችን ባህሪ መከታተል ነው። ቤተክርስቲያን ልትተክሉ ያሰባችሁበት ስፍራ ሂዱና ከ 15 — 20 የሚሆኑ ሰዎችን አነጋሯ፤ በዚህም የሚከተለውን ተማሯ፤ ሞክሯ፡-

ሀ. ስለ እግዚአብሔር ያለው አመለካከት፡- ሰዎች በእግዚአብሔር ያምናሉ? ስለእግዚአብሔር ምንድን ነው የሚያምኑት? ስለእርሱስ ምን ያውቃሉ? በመንግስተ ሰማይ እና በገሃነም መኖር ያምናሉ? በመላዕክት ወይንም በሰይጣን እና አጋንንት መኖር ያምናሉ? ሲታመሙ እና ሲቸገሯ ወዴት ነው እርዳታ ለማግኘት የሚሄዱት? በእድል ያምናሉ? ሲመጣ ያለውን ማንኛውን የወደፊት ጉዳይ መቆጣጠር እንደሚችሉና ለልጆቻቸው የተሻለ አለም መስራት እንደሚችሉ ያምናሉ? ኃጢአት ለእነርሱ ምንድን ነው? ቤተክርስቲያን በቋሚነት ይሄዳሉ? የሚሄዱ ከሆነ በየስንት ጊዜው? የማይሄዱ ከሆነ ለምን?

ለ. ቤተክርስቲያን ልትተክሉበት ያሰባችሁት አካባቢ የሚከበሯ ታላላቅ የህዝብ በአላት ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ነው ነዋሪዎች የሚያከብሯቸው?

ሐ. እርግጠኛ የሆኑበት እና የሚወዱት የሕይወት ክፍል ምንድን ነው? ምንድን ነው አንድ መስወጥ የሚችሉት ጉዳይ?

ሰ. በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚያዩት አንድ ወይንም ሁለት ችግር ምንድን ነው? (ለምሳሌ፡- የመጠጥ ሱስ፣ ወላጅ አልባ ህጻናት፣ የህክምና ሰጪ ተቋማት አለመኖር፣ ጧሪ የሌላቸው አዛውንቶች፣ ስራ አጥነት ወ.ዘ.ተ...)

ሸ. በጣም የሚወዷቸው ሶስት ታሪኮች ምን ምን ናቸው? ታሪኮችን በመንተራስ ሰዎች ስላላቸው እሴት እና የህሊና ህግ እንዲሁም ሕይወትን ስለሚመለከቱበት ጉዳይ ለመወያየት ይቻላል።

ቀ. በማህበረሰቡ የሚታወቁ መሪዎች እነማን ናቸው? ለምንድን ነው እንደመሪ የሚታዩት?

በ. እንደ ጀግና የሚቆጠሩትስ እነማን ናቸው?

ተ. በሌሎች ሰዎች ላይ እንዲያዩት የሚፈልጉት አምስት እሴቶች ምንድን ናቸው (ለምሳሌ፡- ሃቀኝነት፣ ቅልጥፍና፣ ለጋስነት ወ.ዘ.ተ...)

**ደረጃ 4፡- ስለመኸሩ መስክ እና ስለመኸሩ ሰራተኞች የተሰበሰበን መረጃ <u>መተንተን</u>**

አንድ ቤተክርስቲያን ለአንድ ሺህ ሰው ያስፈልጋል በሚለው ከተስማማን፤ እኛ ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰብንበት ማህበረሰብ ወንድ፣ ሴት እና ልጆች ወንጌልን እንዲሰሙ እና እንዲገነዘቡ ባህላቸው በሚፈቅደው መንገድ ለማድረስ ምን ያህል ቤተክርስቲያናት ያስፈልጋሉ?

አንድ ጊዜ መረጃዎችን ከሰበሰብክ፣ የጥናትህን ጠቅላላ አሳብ ጽሑፍ ካሰፈርክና በካርታህ ላይ ማስታወሻ ከጻፍክ በኋላ፤ ጥናትህን ደግመህ ለማየት፣ ለማሰብ እና ባገኘኸው መረጃ መሰረት ለመጸለይ ጊዜ ውሰድ፡፡ እግዚአብሔር አንተ ለታገለግልበት በመረጥከው ስፍራ የሚራራላቸውን መራራት በአንተ ውስጥ እንዲያኖር፤ የእግዚአብሔርንም ፍቅር ለእነርሱ መግለጥ የምትችልበት ምርጥ መንገድ እንዲያሳይህ ጸልይ፡፡ መረጃን መተንተን የዚህ ደረጃ ጭብጥ እንደመሆኑ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመመለስ የሰበሰብከውን መረጃ ተንትን፡-

ሀ. አንተ በመረጥከው የአገልግሎት ስፍራ የታላቁን ተልዕኮ እቅድ ከግብ ለማድረስ ምን ያህል ቤተክርስቲያናት ያስፈልጋሉ? ቤተክርስቲያን ለመትከል ያሰብክበት ማህበረሰብ ወንድ፣ ሴት እና ልጆች ወንጌልን እንዲሰሙ እና እንዲገነዘቡ ባህላቸው በሚፈቅደው መንገድ ለማድረስ ምን ያህል ቤተክርስቲያናት ያስፈልጋሉ? ከዚያም እግዚአብሔር የሚፈልገው በአንተ አገልግሎት እና ለአገልግሎት በመረጥከው ስፍራ ይፈጸም ዘንድ መጸለይ ጀምር፡፡

ለ. ድርሻህን ወስን፡- በዚህ ስፍራ ምን ያህል ቤተክርስቲያን ለመትከል እንደሚያስችልህ በእግዚአብሔር ታምናለህ?

መ. የምትጀምርበትን ስፍራ ምረጥ፡- የት ነው የምትጀምረው? በየትኛው አካባቢ ያሉ ሰዎች ናቸው ለወንጌል በተሻለ ልባቸውን የሚሰጡ? ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ ለወንጌል የተዘጋጀ

ሰብ ያላቸውን ሰዎች ያገኘ የነበረው በምኩራብ ነበር፤ ከዚያ ይጀምርና የሕብረት መረቡን በመዘርጋት በዚህ ህብረት በመጠቀም ተግባሩን ይከውናል (ደቀመዝሙር ያደርጋል)።

ሰ. ስለተህን ምረጥ፡- ማህበረሰቡ እንደ ችግር ያነሳቸው ሁለት ታላላቅ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ምን አይነት ስልት ትጠቀማለህ? በዚያ አካባቢ ቀድመው የተተከሉ ቤተክርስቲያናት የሰዎችን ችግር ለመፍታት ተጠቀመውበት ውጤታማ ያደረጋቸው ስልት ምንድን ነው? ለዚህ ስልት ጠቃሚ የሆኑ ምን አይነት ግብአቶች አሉ? አንተስ ምን አይነት ስጦታ እና ችሎታ አለህ፤ ይህንስ ተጠቀመህ ምን ልትሰራ ትችላለህ?

ረ. ያለህን ግብአት አረጋግጥ፡- ከአንተ ጋር ተመሳሳይ ራዕይ የሚጋራ ሰው አለ? ራዕይህን ስታካፍላቸው እና ያስቀመጥከው ግብ ጋር ለመድረስ በጋራ ለመስራት የሚፈቅዱ ሰዎች አሉ? ምን አይነት የሰው፣ የገንዘብ እና የተለያዩ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎች እንደግብአት አለህ? በዚያ አካባቢ ያሉ ቤተክርስቲያናት ለወንጌል ስርጭት እና ለቤተክርስቲያን ተከላ ፍላጎት አላቸው? አንተ ቤተክርስቲያን ለመትከል በምታደርገው ጥረት ውስጥ አብረውህ ለመስራት ፈቃደኛ ናቸው? ለቤተክርስቲያን ተከላ እና ለወንጌል ስርጭት ከአንተ ጋር ለመስራት እና በዚህም እግዚአብሔር ማንነቱን ለዚህ ማህበረሰብ እንዲያሳውቅ ለመጸለይ ፈቃደኛ ናቸው?

ሸ. ሰዎች ስለእግዚአብሔር ወይንም ስለኢየሱስ ክርስቶስ መረዳቱ አላቸው? ወንጌልን ለሰዎች ስትሰብክ ከየትኛው የወንጌል ክፍል ነው የምትጀምረው? (ምሳሌ፡- የምትጀምረው ከኢየሱስ ክርስቶስ እና ከማዳን ስራው ነው ወይንስ ከሁሉ በላይ ከሆነው አለማትን ከፈጠረው እግዚአብሔር አምላክ በማስተዋወቅ?)

ደረጃ 5፡- ከጥናት እና ምርምሩ (መንፈሳዊ ካርታ መስራት) ሂደት የተማርከው <u>ትምህርት</u>፡-

ይህን የጥናት እና ምርምር (መንፈሳዊ ካርታ መስራት) የቤት ስራህን በምትሰራበት ወቅት ስላገኘኸው ልምድ አሳብህን በዝርዝር ለሌሎች አካፍል። በዚህ የጥናትና ምርምር የቤት ስራ እግዚአብሔር ስለራስህ እና ቤተክርስቲያን ለመትከል ስለተነሳሳህበት ፍላጎት ምን አስተማረህ? ይህን ጥናት እና ምርምር በምታደርግበት ወቅት ምን አይነት ተግዳሮት ገጠመህ? እንዴትስ ይህን

ተግዳሮት ተወጣኸው? ይህን ጥናት እና ምርምር በመስራቱ ረገድ በጣም ቀላል ያለው ተግባር ምን ነበር? ይህን ጥናት እና ምርምር ደግመህ ስራው ብትባል የትኞቹን የጥናት ሂደት በተሻለ ትሰራ ነበር?

**ደረጃ 6፡- ስለመንፈሳዊ ካርታ ጥናትና ምርምር የተገኘን ውጤት ማሳወቅ**

በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርት የጥናትና ምርምር ውጤትህን ስለምታሳውቅ (ሪፖርት ስለምታደርግ) ከወዲሁ ተዘጋጅ፡፡ ሪፖርትህ ከ10-15 ደቂቃ የሚፈጅ መሆን ሲኖርበት የሚከተሉትንም መረጃዎች መያዝ ይጠበቅበታል፡-

1) ክፍል አንድ፡- የተሰበሰቡ መሰረታዊ መረጃዎች (ከ5-7 ደቂቃ)
   ለአገልግሎት ስለመረጥከው ስፍራ ገላጻ አድርግ፡፡
   እንዴት ነበር መረጃህን የሰበሰብከው (በዳሰሳ፣ መደበኛ ባልሆነ ቃለመጠይቅ፣ ምልከታ/በካርታ ላይ ማስፈር፣ ቤተመጽሐፍት የሚገኙ መጽሐፍትን በመጠቀም ወ.ዘ.ተ...)?
   በዚህ ጥናት ውስጥ ስለገጠሙህ ተግዳሮቶች እና እንዴት እንደተወጣሃቸው አስረዳ፡፡
   በሚቀጥለው ጊዜ አሁን ከሰራኸው በተለየ ምን ልትሰራ ትችላለህ?

2) ክፍል ሁለት፡- የጥናት እና ምርምሬ (መንፈሳዊ ካርታ ማዘጋጀት) ትንተና መረጃ (5-8 ደቂቃ)
   ቀሪው ጊዜ የጥናት እና ምርምር ውጤትህን ለማቅረብ ተጠቀምበት፡፡ የምታቀርበው ውጤት የሚከተሉትን አሳቦች መያዝ ይጠበቅበታል፡-
   - ቤተክርስቲያን ለመትከል ስለመረጥከው ስፍራ የተማርከው አስገራሚ መረጃ ምንድን ነው?
   - ያስደነቀህስ መረጃ አለ?
   - ቤተክርስቲያን ለመትከል ስለመረጥከው ስፍራ የተማርከው ለየት ያለና ዕቅድህን ለመወሰን እድል የሰጠህ ነገር አለ?

- ከዚህ ቀደም ስለመረጥከው የመኸር መስክ የምታውቀው እና በዚህ ጥናት ይህ ዕውቀት ትክክል እንደሆነ ያረጋገጥከው እውነት አለ?
- ከዚህ ቀደም የማታውቀው እና በዚህ ጥናትና ምርምር ያወቅኸው፤ ስለመረጥከው ስፍራ ያገኘኸው አዲስ እውቀት አለ?
- ወንጌልን ለማድረስ የሚረዳ ምን አይነት የተከፈተ በር እንዳለ አስተውለሃል? ምን አይነት ተግዳሮቶችን ተመልክተሃል እንዴትስ ሊወገዱ ይችላሉ?
- የተደራጀ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ የቤተክርስቲያን ተከላ በመረጥከው ስፍራ ለመከወን ምን አይነት ተጨማሪ ጥናቶች መደረግ እንዳለባቸው ተመክራለህ?

**የመጠይቅ ናሙና፡-**

ከዚህ በታች ሁለት የመጠይቅ ናሙናዎች ቀርበዋል፡-

(1) በመረጥነው አካባቢ ያሉ ቤተክርስቲያናትን አንድ በአንድ ለማጥናት እና (2) የመረጥነውን አካባቢ ለማጥናት የሚረዳ የመጠይቅ ናሙና፡፡ እነዚህ ለምሳሌነት ብቻ የቀረቡ ስለሆነ እንደየአስፈላጊነቱ ማሻሻል እና መቀየር ይቻላል፡፡

## የአጥቢያ ቤተክርስቲያናት ዳሰሳ

**ሀ. ፕሮፋይል**

የቤተክርስቲያኒቱ ስም

______________________________

ቤተእምነት (ትውፊት)

______________________________

የቤተክርስቲያኒቱ አድራሻ

______________________________

የቤተክርስቲያኒቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ፡- የቤተክርስቲያኒቱ ንብረት ነው________ ኪራይ ነው________

የተመሰረተበት ጊዜ________________________የተመዘገበበት ጊዜ________________________

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ/መሪ ስም

________________________________________እድሜ____________________________

የቤተክርስቲያኑ መጋቢ በሌላ የሙያ ዘርፍ ይሰራል? አዎን__________አይሳተፍም________

በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋ____________________

ሌሎች ቋንቋዎች አሉ? ______________________________________________

የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ብዛት__________________________

በቋሚነት የቤተክርስቲያኒቱን ፕሮግራም የሚካፈሉ ሰዎች ባማካይ ____________________

ለ. ሰዎች

የሚከተለውን መደቦች ሲሞሉ የሚችሉ ሰዎች ቁጥርን ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ መዝግብ፡-

| እድሜ | ፕሮግራም የሚካፈሉ | | አማኞች | | አባላት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| 0 -10 | | | | | | |
| 11 - 17 | | | | | | |
| 18 - 24 | | | | | | |
| 25 - 30 | | | | | | |
| 31 - 55 | | | | | | |
| 55+ | | | | | | |

*የቤተክርስቲያን መላ ምት፡-*

- ሁሉም የፕሮግራም ተካፋዮች አባላት አይደሉም
- ፕሮግራም የሚካፈለው ሰው ቁጥር ከአማኙና ከአባላቱ ይበልጣል
- አንድ ፕሮግራም የሚካፈል ሰው አማኝ ሊሆን ይችላል ይህ ማለት ግን የግድ አባል ነው ማለት አይደለም
- የአማኙ ቁጥር ፕሮግራም ከሚካፈለው ሰው ቁጥር ማነስ ከአባላቱ ደግሞ መብለጥ አለበት፡፡

የተጠመቁ ሰዎች ቁጥር፡- 2014_____ 15_________ 16_______17________18___ 19_________________2020____

ቤተክርስቲያን የሚካፈሉ ቤተሰቦች (ባል/ሚስት) ብዛት፡ ________

መ. መርሃግብር (ፕሮግራም)

**ከዚህ በታች ያሉትን በቤተክርስቲያናት የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን ዝርዝር በመጠቀም በእያንዳንዱ ፕሮግራም የሚሳተፈውን ሰው ብዛት መዝግብ፡፡**

| **ፕሮግራሞች** | **የቤተክርስቲያኒቱ ፕሮግራም መከታተያ፡-** | **የተሳታፊዎች ብዛት** |
|---|---|---|
| ሰንበት ትምህርት (በእድሜ የተከፋፈለ) | | |
| አምልኮ | | |
| የወጣቶች አገልግሎት | | |
| የልጆች አገልግሎት | | |
| የሴቶች አገልግሎት | | |
| የወንዶች አገልግሎት | | |
| ተልዕኮ | | |
| የወንጌል ስርጭት | | |
| የደቀመዝሙርነት ስልጠና | | |
| የቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት | | |
| አዳዲስ ሰዎችን የማስተማር ስልጠና | | |
| የመሪነት ስልጠና | | |
| የአስተማሪዎች ስልጠና | | |
| የጸሎት ህብረት | | |
| ኳየር | | |
| ወታደሮችን ማገልገል | | |
| የአዳዲስ ቤተክርስቲያናት አገልግሎት | | |
| የድራማና ስነጽሁፍ አገልግሎት | | |
| የቴሌቪዥን/ራዲዮ አገልግሎት | | |
| የታራሚዎች (እስረኞች) አገልግሎት | | |
| በሱስ የተጠቁ ሰዎችን የማዳን አገልግሎት | | |
| የሆስፒታል አገልግሎት | | |
| ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናትን የመደገፍ አገልግሎት | | |
| አረጋውያንን በኑሯቸው የመደገፍ አገልግሎት | | |
| የጸሎት አገልግሎት | | |

## ሰ. እቅድ

1. ለዚህ አመት ብቻ ተብሎ በልዩነት የተዘጋጀ የአገልግሎት እቅድ አላችሁ?

አዎን______ የለም____

እቅዶቹስ ምን ምን ናቸው?

---

---

2. ለቀጣይ አመት ተብሎ የተያዘው እቅድ ተጀምሯል?

አዎን______ የለም________

እነዚህስ እቅዶች ምንድን ናቸው

---

---

3. ለቤተክርስቲያኒቱ እቅድን የሚያወጣላት የመሪዎች ቡድን አለ?

አዎን________ የለም____________

4. ቤተክርስቲያኒቱ ዓላማዋን የሚያሳውቅ ግልጽ ጽሑፍ አላት?

አዎን________ የለም____________

5. ቤተክርስቲያኒቱ ገንዘብን የሚመለከት እቅድ አላት?

አዎን________ የለም____________

6. አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደጋቸውን የምትከታተልበት እቅድ አላት?

አዎን________ የለም____________



7. ቤተክርስቲያኒቱ ከሌሎች ቤተክርስቲያናት ጋር በትብብር ትሰራለች?

አዎን________ የለም____________

8. ቤተክርስቲያኒቱ ከሌሎች ቤተእምነቶች ጋር በትብብር ትሰራለች?

አዎን__________ የለም_____________

የተመረጠው ሰፍራ ወይንም "ክበብ" ዳሰሳ ጥናት

ሀ. ማን?

1. በዚህ ቤተክርስቲያን ለየት ባለ መልኩ "ተጽዕኖአቸው ከፍ ያለ" ሰዎች ስብስብ አለ?

2. ከእነዚህ "ተጽዕኖአቸው ከፍ ካለ" ሰዎች በአንድ አይነት የኑሮ ደረጃ ያሉ ይበዛሉ?

አዎን______ የለም______

መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ የትኛው የኑሮ ደረጃ?

ለ. ምን?

1. ቤተክርስቲያኒቱ በምትተከልበት ስፍራ የሚገኝ አስገራሚ ባህሪያት ምንድን ነው?

2. በአከባቢው ያሉ ሰዎች የሚያከብሯት ክብረበዓል፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ብቻ የሚታወቅ በዓል፣ ወይንም ሁሉም የሚያከብሯት ጉዳይ ምንድን ነው?

3. በዚህ አካባቢ ያሉ ሰዎችን የሚገፉ ፍላጎት ምንድን ነው?

ኢኮኖሚ________መንፈሳዊ________ሞራል________ማህበራዊ______የቀለም ትምህርት______ባህል . ቤተሰብ______ኃይማኖት________.

4. በዚህ አካባቢ ምን አይነት የኃይማኖት ቡድኖች አሉ እያንዳንዳቸውስ ምን (ብዛት ደጠቀስ) ያህል ቤተክርስቲያናት አላቸው?

ኦርቶዶክስ______ መጥምቃውያን______ጴንጤቆስጤ______ሮማን ካቶሊክ________ሉተራን
.

ሌሎች የፕሮቴስታንት እምነቶች_______ቤተእምነት የሌላቸው_______ሙስሊም_______የውጭ አገራት ተልዕኮ ቡድኖች_______.

(እባክህን ከዚህ በታች ባለው ስፍራ እንዲህ ያሉ ቡድኖች ካሉ ምን እንደሆኑ መዝግብ፡- ______

______________________________________________________________)

5. ቤተክርስቲያን የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላት እየሰራች ነው?

አዎን_____ የለም_____

መልሳችሁ አዎን ከሆነ አካባቢውን ለማገልገል ቤተክርስቲያን እየሰራች ያለችው አንድ በልዩነት የሚታወቅ ጉዳይ ምንድን ነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

6. የቤተክርስቲያኒቱ መሪ ዓላማ የአካባቢውን ፍላጎት ለማድረስ የሚሆን ደዘት ተካቶበት የተዘጋጀ ነው?

አዎን_____ የለም_____

7. የቤተክርስቲያኒቱ የአገልግሎት እቅድ የአካባቢውን ፍላጎት ከግምት ውስጥ አስገብቶ ነው የታቀደው?

አዎን_____ የለም_____

መ. እንዴት?

1. ቤተክርስቲያን በአካባቢው ካሉ ሰዎች ጋር የቤተሰብነት ስሜት ያለው ግንኙነት አላት?

አዎን________. የለም__________.

መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ እንዴት?

______________________________________________________________

________________________________________________________________

መልሳችሁ "የለም" ከሆነ ከዚህ አካባቢ ጋር የቤተሰብነት ስሜትን ለመፍጠር ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ ይጠበቅባታል?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. የቤተክርስቲያኒቱ ተግባራት አካባቢውን ለመድረስ ታስቦባቸው የቀረቡ ናቸው?

አዎን_________. የለም_________.

3. ቤተክርስቲያኒቱ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች የፕሮቴስታንት እምነት ክፍሎች ጋር ምን አይነት ግንኙነት አላት?

ከሁሉም ጋር መልካም ግንኙነት አላት______.

ከአንዳንዶቹ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ሲኖራት ከሌሎች ጋር እምብዛም የላትም______.

ከየትኛውም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላትም______.

ሰ. ግብአት

1. ለቤተክርስቲያን የሚሆን በአካባቢው የሚገኝ ምን አይነት ግብአት አለ? (ያገኛሉ የምትላቸው ላይ ምልክት አኑር)

ቲቪ/ሬዲዮ______ ስነጽሑፍ______ መጽሐፍ አታሚዎች_____ ለቤተክርስቲያን "እርዳታ" የሚሆን የታወቀ ፈቃድ______ ከዚህ አገልግሎት ጋር በትብብር መስራት የሚችሉ ሌሎች የፕሮቴስታንት እምነት ክፍሎች (አጥቢያ ቤተክርስቲያናት)________ መሰረታቸው ከአገር ውጪ የሆነ የተልዕኮ ድርጅቶች______ የአገልግሎት ቡድኖች______ የተለያዩ ማዕከላት______ የህብረተሰብ ተቋማት_____. የትምህርት ማዕከላት______.

2. በአሁን ወቅት ቤተክርስቲያን በትብብር የምትሰራበት የአገልግሎት መርሃግብር አለ?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

3. አካባቢውን በተመለከተ ቤተክርስቲያኒቱ ከሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ጋር በአካባቢው ያሉና ያልዳኑ ነፍሳትን በተመለከተ ውይይት እያደረገች ነው?

አዎን__________. የለም___________.

4. የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች በአካባቢው ያሉ ሰዎችን ሁሉ ለክርስቶስ ለመማረክ ከሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያናት እና ድርጅቶች ጋር ለመስራት ፈቃደኛ ናቸው?

አዎን____________.　　　　　　የለም____________.

መልሳችሁ "አዎን" ከሆነ መቼ ነው "በአካባቢው ያለውን ግብአት" ለመሰብሰብ እና በአካባቢው ላይ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ የወንጌል ተልዕኮን ለመፈጸም ተነጋግረዋል?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

መልሳችሁ "የለም" ከሆነ ለምን?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

# ክፍል ትምህርት 2

## ክርስቶስ ለእኔ ያደረገልኝ ይህን ነው! የግል የሕይወት ምስክርነታችሁን ማደራጀት እና ለሌሎች መንገር (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ጠቅላላውን ሰልጣኝ የሚሳተፉበት ስለምስክርነት እና የምስክርነት ጥቅም ለመረዳት ጋብዝ፡፡ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍል በመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ ተሳታፊዎች ለጠቅላላው ቡድን እንዲያነብቡት አድርግ፤ ከዚያም የተነበቡት የቃለ እግዚአብሔር ክፍሎች ለውይይቱ መሰረት ይሆናሉ፡፡ (10 ደቂቃ)

**የምስክርነት ባህሪ**

ሀ. ምስክር ለመሆን የተጠራነው (ሐዋ 1:8)

ለ. ምስክርነት ለመስጠት ነው የተጠራነው (ሐዋ 10:42)

የመስክርነት ዋጋ

ሀ. ወንጌል ላይ የሚደርስን ተቃውሞ መቋቋም (የግል ምስክርነት ሐዋ 26:12-18)

ለ. በመንፈሳዊ ውጊያ ሰይጣንን ድል መንሳት (ራእ 12:10-12)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከተሳታፊዎች ጋር ስለግል ሕይወት ምስክርነት ቁልፍ ይዘቶች ተወያይ

- ጠቅላላውን ተሳታፊ በሶስት ቡድን በመክፈል ከዚህ በታች የቀረቡትን የምስክርነት ናሙና ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች እንዲያወጡ፤ ከዚህ ክፍል ያገኙትን ቁልፍ ምስክርነት ደዘት እንዲለዩ አበረታታ፡፡ (10 ደቂቃ)

**ምስክርነትን ማዘጋጀት፡- ቁልፍ ደዘት**

1. ክርስቶስን ከመቀበልህ <u>በፊት</u> የነበረው ሕይወትህ ምን ይመስላል?

2. <u>እንዴት</u> ነው ክርስቶስን ያወቅከው?

3. ክርስቶስን ማወቅህስ እንዴት ሕይወትህን <u>ቀየረው</u>?

## ስለምስክርነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌች

- እውር ሆኖ የተወለደው ሰው (ዮሐ 9፡13-34)
- በንጉስ አግሪጳ ፊት ጳውሎስ የመሰከረው ምስክርነት (ሐዋ 26፡1-31)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ከዚህ በታች የግል ሕይወት ምስክርነት ስለመስጠት የቀረበውን መምሪያ ከተሳታፊዎች ጋር ክለሳ አድርጉ፡፡
- ሰልጣኞቹም የራሳቸውን የግል ሕይወት ምስክርነት ከታች በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት እንዲያዘጋጁ 15 ደቂቃ ስጣቸው፡፡
- በዚህም ተሳታፊዎች በዚህች አጭር ጊዜ የሚሰሩት የግል ሕይወት ምስክርነት የመጀመሪያ ስራ ብቻ (ግርድፍ ጽሑፍ) እንዲያዘጋጁ እንደሆነ አስረግጠህ ተናገር፡፡ ታዲያ ይህን ግርድፍ ጽሑፍ ለቤተክርስቲያን ተከሳ አውድ ከመጠቀማቸው በፊት አጥርተው እንደገና መጻፍ የሚችሉበት እድል እንዳላቸው አስረዳ፡፡

- ተሳታፊዎችን በሙሉ ሶስት ሶስት እየሆኑ ቡድን እንዲሰሩ አድርግ፤ ከዚያም በዚህ ቡድን ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው ለቡድኑ የግል ሕይወት ምስክርነቱን 5 እና ከዚያ ያነሰ ደቂቃ በመውሰድ እንዲያካፍል አድርግ፡፡

ከዚህ በታች በተቀመጠው ክፍት ቦታ የግል ሕይወት ምስክርነት ቀለፍ ይዘት ለመጻፍ የተቀመጠውን ማውጫ ተከትላችሁ የግል ሕይወት ምስክርነታችሁን አስፍሩ፡፡ (1) ሶስቱንም ይዘቶች መጠቀም፣ (2) ለመረዳት በጣም ቀላል ነው፣ (3) ትኩረታችሁን በመልካሙ የምስራች (ኢየሱስ ለእኔ ያደረገውን ለአንተም ሊደርግልህ ይችላል!) እና (4) አጠር ያለ ጊዜ የሚወስድ ነው - ለሰው የምትነግረው ምስክርነት 5 ወይንም ከዚያ ያነሰ ደቂቃ የሚፈጅ መሆን አለበት፡፡

**ኢየሱስ ለእኔ ያደረገው፡- የግል ሕይወት ምስክርነቴ**

ኢየሱስን ከማግኘቴ በፊት ሕይወቴ ምን ይመስል እንደነበር፡-

________________________________________________________________________

______________________________________________________________

ኢየሱስን እንዴት ተዋወቅሁ፡-

________________________________________________________________________

______________________________________________________________

ኢየሱስን ማወቁ ሕይወቴን እንዴት እንደቀየረው፡-

________________________________________________________________________

______________________________________________________________

## ለሞጁል 3 የሚሆን የትግበራ እቅድ

## የግል ሕይወት ምስክርነትህን በጌታ ለማያምኑ አምስት ሰዎች ተናገር (5 ደቂቃ)

ቀጣዩን ክፍለትምህርት ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተሉትን የተግበራ ደረጃዎች አጠናቁ፡-

- "የግል የህይወት ታሪክን ማዘጋጀትና ማካፈል" በሚለው ርዕስ ስር የጀመራችሁትን የግል ሕይወት ምስክርነት ጽሑፍ በተቀመጠው መምሪያ መሰረት አጥርታችሁ ለመጻፍ ጊዜ ውሰዱ
- የራሳችሁን ምስክርነት ለብቻችሁ በምትሆኑበት ጊዜ ልክ ለሰው እነደምታቀርቡ እያሰባችሁ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ማቅረብን ተለማመዱ፡፡
- እግዚአብሔር "መለኮታዊ የሆነ መገጣጠም" ይህን መስክርነት ለማት ከሚያስፈልገው ሰው ጋር በሚመጡት አራት ሳምንታት ውስጥ (ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ) እንዲያገጣጥማችሁ ጸልዩ፡፡
- ይህን ምስክርነት ቀድማችሁ ቢያንስ ለሶስት ክርስቲያን ወገኖች በመንገር ምስክርነትህ ለሰዎች የሚገባ እንደሆነና እንዳልሆነ አረጋግጥ፡፡
- ለአምስት ጌታን ለማያውቁ ጓደኞች ወይንም በመጪው ሳምነት ለምታገኛቸው ቁልፍ ሰዎች አካፍል፡፡ የሚቀጥለው ስልጠና ክፍለ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ለአገልግሎት በመረጥከው ስፍራ ላሉ አምስት ጌታን ለማያውቁ ሰዎች ምስክርነትህን ተናገር፡፡
- ሰዎችን ስትጎበኝ ከአንተ ጋር ያለ አንድ አማኝን በአንተ ስር እንዲለ የማማከርና ድጋፍ ተገልጋይ ይዘህ ሂድ፡፡
- ምስክርነትህን በሚቀጥለው ስልጠና ወይንም ክፍለትምህርት ለማቅረብ ተዘጋጅ፡፡

# ክፍለትምህርት 3

# ትናንሽ ቡድኖችን መምራት (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ከዚህ በታች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የቀረበውን የመሪነት ጽንሰ ሐሳብ በተመሰከተ ገለጻ ስታደርግ ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃል እንዲሞሉ ንገራቸው፡፡ ጠቅላላውን ተሳታፊ ያማከለ፤ ከዚህ በታች ባሉ ጥያቄዎች በመጠቀም ስለተጠቀሱት ጽንሰ ሐሳቦችን በተመለከተ ውይይት አድርግ፡፡

**ጠቅለል ያለ የመሪነት ጽንሰ ሐሳብ** (20 ደቂቃ)

1. የክርስትና ሕይወትን <u>በኑሮ ማሳየት</u>

- በአዲስ ኪዳን መሪነት ውስጥ በኑሮ ማሳየት (ሞዴል መሆን) ምን አይነት ሚና ነበረው? 1ተሰ 1፡6-7፤ 1ቆሮ 11፡1

2. አዳዲስ መሪዎችን <u>ማብቃት</u>

- የተግባር ስልጠና እየወሰደ ያለ መሪ ለትናንሽ ቡድኖች ምንድን ነው?
- የትናንሽ ቡድኖች መሪ በቀጣይ መሪ ለመሆን የሚመርጠው ሰው ምን አይነት ባህሪያትን መመልከት ይኖርበታል?
- የትናንሽ ቡድኖች መሪ በሚመራው ቡድን ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች በሙሉ ኃላፊነት መስጠት ይጠበቅበታል ወይንስ በቀጣይ መሪ ይሆናል ብሎ ላሰበው ሰው ብቻ ነው ኃላፊነት መስጠት ያለበት? ለምን ወይንም ለምን ለእርሱ ብቻ መስጠት የለበትም?
- በመሪነት ሲሰለጥን የሚገባውን ሰው ለመምረጥ የትናንሽ ቡድኖች መሪ ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ ይገባዋል?

- አዲስ የተመረጠው መሪ በቀጣይ የራሱን ቡድን ይዞ ማስጠናት እስኪጀምር ድረስ ምን አይነት ተግባራትን ከመሪው ጋር ያከናውናል?

3. <u>ማስታጠቅ</u> እና ለአገልግሎት <u>ማሰማራት</u>

- ትናንሽ ቡድኖች አዳዲስ መሪዎች በውስጣቸው እንዲፈጠር እድል በመስጠት ለመሪነት በር ይከፍታሉ፡፡ አንድ መሪ በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ ከሚሰጠው ኃላፊነት ምን አይነት ነገሮችን ሊማር ይችላል? ምሳሌ ስጥ፡፡

## የቡድን ጥናትን መምራት (5 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** የሚከተለውን ትምህርት በቃል በምታስተምርበት ወቅት ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ያለውን ክፍት ስፍራ በተገቢው ቃል እንዲሞሉ አበረታታቸው፡፡ በዚህ ክፍለትምህርት መጨረሻ የቀረበውን የግብአት ዝርዝር ለተሳታፊዎች መጠቀምህን አትዘንጋ፡፡

(1) ለቡድን ጥናት የሚሆን ዝምታ መስበሪያ፣ (2) የቡድን ውይይቱ ይጀመራል እና (3) በቡድን ጣናት ወቅት የሚኖረ ተግባራት ምሳሌ

**እንዲህ በል** "ትክክለኛ የትናንሽ ቡድኖች ጥናት ሁልጊዜ ያለመዛነፍ የሚመጡ ብዙ አይነት ይዘቶች አሉት፤ እነዚህን ይዘቶች በመጡበት/በሚከሰቱበት ቅደም ተከተል አቀርብላችኋለሁ"

1. በቡድኑ አባላት መካከል የሚኖር <u>መሰባሰብ</u>

2. ጸሎት፣ መዝሙርና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን <u>አምልኮ</u>

3. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት</u>ና ውይይት

4. አገልግሎቱን ማስፋት፤ የቡድኑ ተሳታፊዎች የግል እና የቡድን ተግባራትን በማቀናጀት ጓደኞቻቸውን፣ ጎረቤቶቻቸውን እና ከዚያም ከፋፍ ያለ የማህበረሰብ ክፍል በወንጌል

የሚያርሱበትን እድል ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ያልተቀሳቀሱ ሰዎች ይመጡ ዘንድ ጸሎት ይደረጋል፡፡

**የጥናት ቡድንን ማስተዳደር (10 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ሁሉም ተሳታፊ ትናንሽ ቡድኖችን የማስተዳደር ጉዳይን በማንሳት እንዲወያዩ አድርግ፤ ለዚህም ውይይት ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መጠቀም ትችላለህ፡፡

- ለምንድን ነው የትናንሽ ቡድን መሪ ለቡድን ጠቀሳሳ የሚሆን እቅድ እና ለእያንዳንዱ የጥናት ቀን የሚሆን እቅድ ለማውጣት ለምን ይጨነቃል? ለምን ቡድኑ "እንዳፈቀደው" የጥናቱ ይዘት በመሪው አቅጣጫ ዝምብሎ አይጓዝም?
- እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ከታች የተዘረዘሩት ፍላጎቶች ይሞሉለት ዘንድ ምን አይነት ዝግጅት ነው መደረግ ያለበት?

  ሀ) መገኛ ስፍራ

  ለ) መሰባሰብ

  መ) አምልኮ

  ሰ) ጸሎት

  ረ) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውይይት

  ሸ) ደቀመዝሙርነት

  ቀ) ወንጌል ስርጭት

- ለምንድን ነው ለእያንዳንዱ አዲስ አማኝ ከጥናት ቡድኑ መንፈሳዊ "አባት/እናት" ተመድቦለት ደቀዝሙር እንዲሆን የሚያስፈልገው?

**የጥናት ቡድኖች ተግባር (25 ደቂቃ)**

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ጠቀሳሳውን ተሳታፊ ከ5-7 ሰው በያዘ ትናንሽ ቡድን ክፈልላቸው፤ ከእነዚህ ውስጥ ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ እንደ ቡድን መሪ አንድ ደግሞ ለመሪነት እንደሚሰለጥን ተማሪ

ሆነው የሚሰሩ ሁለት ሰዎችን በመምረጥ፤ የተቀረው ደግሞ የጥናት ቡድኑ አባል በመሆን ራሳቸውን ያዘጋጁ፡፡ ከዚህ በታች የቀረበውን ትዕዛዝ ለሁሉም አንብብላቸውና ፤ ተሳታፊዎቹ በዚህ ዙሪያ ያላቸውን ጥያቄ ለመመለስ ጊዜ ስጥ፡፡

**መመሪያ፡-**

1. በመጀመሪያ ከዚህ በታች የሰፈረውንና ዝምታን ስለመስበር ከቀረቡት ጨዋታዎች መካከል "እንደማሸንፍህ አታውቅም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጨዋታ አጫውት፡፡

2. ከዚያም ከዚህ በታች ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የቡድን መሪው እና ለመሪነት የሚሰለጥን ለመሆን የተመረጠው ሰው ለውይይት ይሆናሉ ያሏቸውን ጥያቄዎች ይመርጣሉ፡፡ (ከፈለጋችሁ ይህን ጥያቄ መጠቀም ትችላላችሁ፡- በሕይወትህ የተደሰትክበት ቀን እና ምክንያት ምንድን ነው?)

3. ዝምታን የመስበር ጨዋታ ከተጫወቱና ጥናታቸውን ካደረጉ በኋላ፤ የቡድኑ አባላት በሙሉ እንዳሰው ስሌላቸው የሚጸልዩበት ጊዜ ይውሰዱ፡፡

4. የቡድኑ አባላት በጠቅላላ የጥናቱን ይዘትና የቡድኑ አቋም መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡

**በቡድን ጥናት ወቅት ዝምታ ለመስበር የሚረዱ ጨዋታዎች**

"ዝምታ መስበር" ሰዎች ያለምንም ስጋት በጨዋታ መልክ አንዳቸው ሌላቸውን ለማወቅ የሚጠቅም መንገድ ነው፡፡ ዝምታን መስበር በአብዛኛው የሚከወነው አዳዲስ የጥናት ቡድኖች የመጀመሪያ ስብሰባቸውን በሚያደርጉበት ወቅት ነው፡፡ ጥቂት ማስታወሻዎች፡-

- ዝምታን ለመስበር የምንጠቀምበት መንገድ ለቡድኑ የሚመጥን መሆን አለበት፡፡ የምንጠቀምበት ጨዋታ በጣም እንደ ልጅ የሚያደርግ ከሆነ የተሳታፊዎችን ምቾት ይነሳል፤ ከሚገባው በላይ ውስብስብና የሰዎችን አቅም የሚፈታተን ከሆነ የቡድኑ

ተሳታፊዎች ከብሬችው የሚነካ ስለሚመስላቸው ወደዚህ ህብረት ደግመው ሳይመጡ ይችላሉ፡፡

- እንዳዱ ሰው በዚህ ጨዋታ ውስጥ እንዲሳተፍ እንደምትፈልግ በማስረዳት ሁሉም ይሳተፉ ዘንድ አበረታታ፡፡
- አንዳንድ ዝምታን የመስበር ጨዋታዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ሲውሉ ይችላሉ፡፡
- አንዳንድ ጨዋታዎች የሚፈብሻቸው የቡድኑ አባላት ካሉ እነርሱን በችሎታ እንዳትመለከት፤ ሁልጊዜ በንቃት መከታተል ይኖርብሃል፡፡
- የቡድኑ አባላት በጊዜ ሂደት እየተዋወቁ በመጡ ቁጥር ዝምታን ስመስበር እንቅስቃሴ የምንወስደው ጊዜ እያጠረ መሄድ አለበት፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የጥናት ቀናት ምናልባት ለጥናት የመደብከው ጊዜ ግማሹን ዝምታን ስመስበር ትጠቀም እንደሆን ከወሬት በኋላ ግን ዝምታን መስበር የምትጠቀመው ከ10 - 15 ደቂቃ ብቻ ይሆናል፡፡

**እርስ በእርስ ለመተዋወቅ የሚረዱ ጥያቄዎች**

**ከ7-12 አመት እድሜ ልጆች በነበሩችሁ ጊዜ...**

1. የት ነበር የምትኖረው? ምን ያህል ወንድሞ እና እህቶች ነበሩህ?

2. ምን አይነት የትራንስፖርት መገልገያ ነበር ቤተሰቦችህ ይጠቀሙ የነበረው?

3. በጣም ትቀርበው የነበረ ሰው ማን ነው?

4. መቼ ነው እግዚአብሔር ከቃል በዘለለ በግል ሕይወትህ ያወቅኸው?

**እኔ ማን ነኝ?**

ይህን ጨዋታ ለማጫወት መጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘገቡልንን ወይንም ሌሎች ታዋቂ ሰዎችን ስም በወረቀት ላይ በመጻፍ፤ ለጨዋታ የተመረጠው ሰው ጀርባ ላይ ትለጥፈዋለህ፡፡ ይህን

ስታደርግ ተጫዋቹ የሚስጠፍስትን ስም በፍጹም ማየት የስበትም፡፡ ከዚያም ተሳታፊዎችን አንድ ጥያቄ ለአንድ ሰው ስስተስጠፈስት ሰው ማንነት እየጠየቀ ማንነቱን እስኪያውቅ ድረስ ይዞራል፡፡

ይህ ጨዋታ ሁሉም ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን ሰዎች በሚገባ የሚያውቁ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

**እሽንፋስሁ ይህን አታውቁም**

እያንዳንዱ ተሳታፊ በወረቀት ላይ ከዚህ በፊት ለማንም ያልተናገረውን እና ማንም ሰው አያውቀውም ብሎ የሚያስበውን ባህሪያት በወረቀት ላይ ያሰፍራል፡፡ ከዚያም የተጻፈባቸው ወረቀቶች ይሰበሰቡና ተጣጥፈውና ተደበላልቀው በቡድን መሪው አማካኝነት  እንደ እጣ በየተራ እየወጡ እንደየቅደም ተከተላቸው ቁጥር ይሰጣቸዋል፡፡ ቁጥሩ በሚሰጥበት ወቅት የትኛው ሰው የትኛው ቁጥር እንደተሰጠው አያውቅም፡፡ ከዚያም ከተራ ቁጥር አንድ ጀምሮ በወረቀቱ ላይ የሰፈረት ባህሪያት ሲነበቡ ተሳታፊዎች እነዚያ ባህሪያት ሲወክሉት የሚችለውን ሰው በመገመት ስሙን በሚነገረው ተራ ቁጥር መሰረት ይመዘግባል፡፡ ከዚያም በመጨረሻ የተሻለ የገመተው ሰው ወይንም የሰዎችን ባህሬ ከማንነታቸው ጋር በማዛመድ በቁጥር ከፍ ያለ ያስመዘገበው አሸናፊ ይሆናል፡፡

**ትውውቅ**

እያንዳንዱ ሰው በቡድን ውስጥ ተሳታፊ ስሆነ ሌላ ሰው የሚሆን ጥያቄ እንዲያስብ የተወሰኑ ደቂቃዎችን መስጠት፤ ከዚያም ቡድኑን መሪው በሚፈልገው መንገድ በማሰባጠር በአሳባቸው ያዘጋጁትን ጥያቄዎች ለደረሳቸው ሰው በማቅረብ የመሳሹን መልስ እና ስም እንዲጽፉ አድርግ፡፡ አስር ደቂቃ የሚሆን ጊዜ ስመጠያየቅ ከወሰዱ በኋላ ቡድኑን በጋራ በመሰብሰብ እያንዳንዱ ሰው ከጠየቀው ጥያቄ ስስግለሰቡ ያወቀውን እንዲናገር እድል ስጥ፡፡ ጥሩ ጥያቄዎች በፈጠርን ቁጥር አስገራሚ መልሶች እናገኛለን፡፡

## ሁለት እውነትና አንድ ውሸት

እያንዳንዱ የቡድን አባል በተዘጋጀለት ወረቀት ላይ በትልቁ ስለራሱ ሁለት እውነት እና ውሸት ይጽፋል። ሁሉም ሰው ጽፎ እንደጨረሰ፤ ተራ በተራ ወረቀቶቹን በማሳየት አንድ ሰው ሌላው ሰው ስለራሱ የጻፈውን ውሸት ከሁለቱ እውነቶች ለይቶ እንዲናገር ማድረግ። (በዚህ ጨዋታ ለእውነት የቀረበ ውሸት መጻፍ ጨዋታውን ፍትሃዊ አያደርገውምና ሁሉም ሰው የሚጽፈው ውሸት ሊታወቅ የሚችል ቢሆን መልካም ነው።)

## የአየር ሁኔታ ዘገባ

ከመሪው ጀምረህ እያንዳንዱን ሰው በዚህ ወቅት የተሰማውን ስሜት ልክ እንደ አየር ሁኔታ በማስመሰል እንዲገልጽ ማድረግ (ለምሳሌ፡- ከፊል ደመናማ፣ ፀሐያማ ወ.ዘ.ተ…)። ከዚያም ተሳታፊዎች የተሰማቸውን ለመግለጽ ለምን የመረጡትን የአየር ሁኔታ እንደመረጡ እንዲያብራሩ እድል ስጣቸው። መሪው እንዲህ ባለው ሁኔታ የተሰማውን ስሜት በመግለጥ ቀዳሚ ሆኖ ቢያስተዋውቅ አሳቡን በጥልቀት ለመረዳት ይመረጣል።

## አምኖ መጓዝ

ጠቅላላውን ተሳታፊ ሁለት ሁለት አድርጎ በማጣመር፤ አንዱን አይኑን በማሰር ሌላኛው ደግሞ እንደ መሪ በመሆን አይኑን የታሰረውን ሰው የቡድን ጥናቱ በሚደረግበት ቤት ወይንም ቤተክርስቲያን አካባቢ እየመራ በሌላ ሰው ድጋፍ መንቀሳቀስ ምን እንደሚመስል እንዲገነዘቡ ቤቱ ከአንድ በላይ ወለል ያለው (ፎቅ ቤት) ከሆነ ደረጃዎችን እንዲወጣ እና እንዲወርድ፣ ወደውጭ እንዲወጣ፣ የአትክልት ስፍራ ካለ በዚያ እንዲሄድ እና በዚያም እንዲጓዝ ማድረግ፤ መሪው ጉዞውን በሚያደርግበት ወቅት በተለያየ ፍጥነት ወይንም አንዳንድ ጊዜ ዝግ በሌላ ጊዜ ደግሞ ፈጠን በማለት መምራት። እያንዳንዱን መሪ እንዴት መምራት እንዳለበት ምሪት የምትሰጠው ያለምንም ድምጽ በምልክት ብቻ መሆን ይገባዋል። ከአምስት ደቂቃ በኋላ መሪ የነበረው ሰው አይኑን ታስሮ ተመሪ፤ ተመሪ የነበረው ደግሞ መሪ ሆኖ በተመሳሳይ እንዲመራ በማድረግ ልክ እንደመጀመሪያው ሁሉ ለአምስት ደቂቃ ከቆዩ በኋላ ሁሉም ተሳታፊዎች አንድ ላይ እንደገና

እንዲሰበሰቡ በማድረግ፤ አይናቸውን ታስረው ነገሮችን በሚዳስሱበት ወቅት ምን አይነት ስሜት እንደተፈጠረባቸው እንዲናገሩ ይህን ጥያቄ መጠየቅ፤ አይናችሁ በታሰረ ወቅት ስለሚመራችሁ ሰው ምን አይነት ስሜት ተሰማችሁ? አይናችሁን ታስራችሁ በምትጓዙበት ወቅትሙሉ ለሙሉ በሌላ ሰው ላይ ጥገኛ መሆንና እየሆነ ባለው ጉዳይ ላይ ምንም አይነት ውሳኔ መወሰን አለመቻል ምን አይነት ስሜት ይፈጥራል? ስለራስህ ምን ተማርክ? እንዴት ነው ይህን ጨዋታ በአንተና በእግዚአብሔር መካከል ላለ ግንኙነት ምሳሌ የሚሆነው? ከሌሎችስ ጋር ስላለህ ግንኙነትስ ምን ያስተምርሃል?

## የሳንቲም ጨዋታ

ወደ ጥናት ቡድኑ አዳዲስ ሰዎች ከመጡ የሳንቲም ጨዋታን እንደ ዝምታ መስበሪያ መሳሪያ ለመጠቀም ሁሌም በአእምሮ ማኖር አትራፊ ነው፡፡ ጨዋታው እንዲህ ነው፦ ለእያንዳንዱ ተሳታፊ አስር አስር ሳንቲሞችን መስጠት፤ ከዚያም አንድ ሰው ከሌሎቹ የሚለየውን አንድ ነገር በመጥራት ከተሰጡት አስር ሳንቲሞች አንዱን ያስቀምጣል፤ (ለምሳሌ፦ በጉዞ እና የተለያዩ ስፍራዎችን በመጎብኘት የሚታወቅ አንድ ሰው ቢኖር እንዲህ ሊል ይችላል፤ "ሰሜን ተራሮችን ጎብኝቻለሁ፡፡") ከዚያም አንድ ሳንቲም ያስቀምጣል፤ እርሱ ወደሄደበት የሄደ ሌላ ሰው ካለ እርሱም አንድ ሳንቲም ያስቀምጣል እንዲህ እያለ ሁሉንም ሳቲሙን ቀድሞ የጨረሰ ሰው አሸናፊ ይሆናል፡፡

## በቀላሉ ውሸት መሆኑ የሚታወቅ ቡድን

ለዚህ ተግባር ሁለት ቡድን እና ሁለት ክፍሎች ያስፈልጋችኋል፡፡ ጠቅላላውን ተሳታፊ ለሁለት ክፍሉ፤ ከዚያም ቡድን አንድ ለቡድን ሁለት እንዲተገብረው የሚፈልገውን ተግባር ያለምንም ድምጽ በምልክት ብቻ ያሳያል (ለምሳሌ፦ ቁርስ መመገብ)፡፡ ቡድን አንድ ይህን የሚነግረው ለአንድ ሰው ብቻ ነው (ለምሳሌ፦ ይህን ሰው ፀጋ የምትባል ናት እንበል) ከዚያም ከቡድን ሁለት አንድ ሰው ፀጋ ትጠራለች ነገርግን እርሷ ሳለችበት ቡድን ለተሰጠው ተግባር መናገር አይፈቀድም፡፡ ቡድን ሁለት የተመረጠው አንድ ሰው (ለምሳሌ፦ መገርሳ ነው እንበል) መገርሳ ፀጋ

ወዳለችበት ክፍል ሄዳ እርሷ የሰማችውን በተግባር (አስታውሱ ምንም አይነት ድምፅ ማውጣት አይፈቀድም) ታሳየዋለች፡፡ የእርሷም ቡድን ለመገርሳ የምታሳየውን ተግበር ይመለከታሉ፤ ከዚያም ፀጋ ሄዳ ከቡድን ሁለት አንድ ሰው መገርሳ ወዳለበት ክፍል ትልካለች፤ ከዚያም መገርሳ ለዚያ ሰው ያየውን በተግባር ያሳያል፡፡ በመቀጠል መገርሳ ደግሞ ወደሌላኛው ክፍል በመሄድ ከእርሱ ቡድን አንድ ሰው ወደ ሌላኛው ክፍል ይልካል፤ ይህ ተግባር የቡድን ሁለት የመጨረሻው ሰው ይህን ተግባር አስኪመለከት ድረስ ይቀጥላል፡፡ የመጨረሻው ሰው ተግባሩ ምን እንደሆነ መገመት እና በሁሉ ሰው ፊት መናገር አለበት፡፡ ልክ እንዲሁ ቡድን ሁለት ለቡድን አንድ የሚተገበረውን ያዘጋጃል እንደመጀመሪያው ሁሉ ይተገበራል፡፡

### መልሶች እና ጸሐፍት

በወረቀት ላይ አራት ወይንም አምስት የሰውን ማንነት ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎች አለበህ ጻፍ (በፍጹም የሰውን ክብር የሚነካ መሆን የለበትም ለምሳሌ፡- የምትወደው ንብረት ምንድን ነው? አሁን ማድረግ ያልቻልከው እና ብትችል የምታደርገው አንድ ነገር ምንድን ነው? በጣም የምትመኘው የጉብኝት ስፍራ ምንድን ነው?) ሁሉም ተሳታፊ ከተቻለ ሁሉንም ካልሆ ደግሞ ቢያንስ ሶስቱን መመለስ ይኖርበታል፡፡ ተዲያ ጥያቄውን በሚጽፋበትም ሆነ በሚመልሱበት ወቅት ስማቸውን እንዳይጽፋ አስጠንቅቃቸው፡፡ ከዚያም መሪው ወረቀቶቹን ሰብስቦ መልሶችን ለጠቅላላ ቡድን ያንብብ፡፡ ከዚያም ሁሉም የተነበበው ሰው መልስ የማን እንደሆነ ይገምቱ፡፡

### ሁሉም ጎረቤቶቼ

ሁሉም ተሳታፊ ክብ ሰርቶ ይቀመጣል፤ ታዲያ የወንበሩ ቁጥር ከተሳታፊው ቁጥር በአንድ የሚያንስ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚያም ሁሉም ሰው ሲቀመጥ አንደ ሰው ወንበር ስለሚያጣ መቆም ይገደዳል ታዲያ ያ ሰው አንድ ጎረቤት መፈለግ ይጠበቅበታል፡፡ ጎረቤት ለመፈለግ ደግሞ እርሱ ከሌሎች ጋር አንድ የሚያደርገውን ነገር ይፈልጋል፤ (ለምሳሌ፡- ሁሉም ጎረቤቶቼ የምትዘምሩ፤ ወይንም ሁሉም ጎረቤቶቼ ቀኝ እጃችሁን የምትጠቀሙ) ታዲያ በዚህ ጊዜ የቆመው ሰው የጠራው መለያ የሚመለከታቸው ሁሉም በታማኝነት ይቆማሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቀኝ እጃችሁን

የምትጠቀሙ ሲሰ ግራ እጃቸውን ከሚጠቀሙ ወይንም በተሰምደ ግራኝ ከምንላቸው ውጪ ሁሉም ያነሳሉ። ታዲያ የተነሱት ሁሉ በነበሩበት ሳይሆን ሌላ ወንበር ፈልገው ነው መቀመጥ ያለባቸው። በዚህ ጊዜ መሃል የቆመው ሰውም በዚህ መሃል አንድ ወንበር ሲለቀቅ ተሽቀዳድሞ ይይዛል ታዲያ ሁሉም ሰው ሲቀመጥ አንድ ሰው ብቻ ወንበር ያጣል ታዲያ ይህ ሰው እንደመጀመሪየው ሰው መሃል በመቆም፣ ከእርሱ ጋር ተመሰሳይነት ያላቸውን ጎረቤቶቹን በመጥራት ያስቆማል ወንበርም ይፈልጋል እንዲህ እንዲህ እያለ ጨዋታው ይቀጥላል።

## የቡድን ውይይት

ከዚህ በታች ዝምታን ለመስበር ያደረጋችኋቸውን ጨዋታዎች በሚገባ ለመረዳት ግብአት ሲሆኑ የሚችሉ ጥያቄዎች ተዘርዝረዋል። አንድ ማስታዋል የሚገባን ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ለአዳዲስ ቡድኖች የሚሆን ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ከተመሰረተ ለቆየ ቡድን የሚሆን ነው። በአንድ የቡድን ጥናት ውስጥ አንድ ጥያቄ ብቻ መጠቀም ትክክል ነው። ጥያቄዎቹን የሚመረጡበት ዋና ምክንያት አንድም የቡድኑ አባላት እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ መንገድን ለማመቻቸት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የጥናት ክፍሉን በሚገባ ለመረዳት ማገዝ ነው።

1. በሕይወትህ የተደሰትክበት ገጠመኝ ምንድን ነው?
2. በጣም የሚያፅትህ የሕይወት ገጠመኝ ምንድን ነው?
3. እስከዛሬ ከከወንካቸው ተግባራት ሁሉ ከባዱ የትኛው ነው?
4. ከተቀበልካቸው አድናቆቶች (comliment) ትልቅ የምትለው የትኛውን ነው?
5. በምድር ላይ አለኝ የምትለው ምርጥ ጓደኛ ማን ነው? ስለጓደኛህ ጥቂት ተናገር
6. ከቤትህ ካሉ ክፍሎች (ከአንድ በላይ የሆነ ክፍል ውስጥ የምትኖረ እንደሆን) የትኛውን ይበልጥ ትወዳለህ?
7. በሚቀጥለው ሳምንት ልትፈጽመው የምትፈልገው አንድ ጉዳይ ምንድን ነው?
8. በልጅነትህ ደስ ብሎህና ተመችቶህ የምትቀይበት ስፍራ የት ነው?
9. ጊዜን መመለስ የምትችልበት ማሽን ቢኖርህ እና በጊዜ ውስጥ መገኘት ብትችል በታሪክ ወደኋላ ወይም ወደፊት የትኛውን ጊዜ ማየት ትፈልጋለህ?

10. አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረክበት/የከወንክበት ወቅት ትዝ ይልሃል?
11. አንድ ሺህ አመት ማኖር የሚችል መድሃኒት ቢኖር ያንን መድሀኒት ለመውሰድ ፈቃደኛ ትሆናለህ? ለምን?
12. የምትሞትበትን ቀን ማወቅ ትፈልጋለህ?
13. ከዘመዶችህ በሚገባ የምትጠያየቁት ከማን ጋር ነው? ለምን?
14. ከአባትህ ጋር ያሳለፍከው እና የማትረሳው ምርጥ ጊዜ መቼ ነው? ከእናትህ ጋር ያሳለፍከውስ?
15. ኢየሱስ የሕይወትህ ጌታ እንዲሆን እስከመምረጥ ያደረሰህና እግዚአብሔር ለዚህ ስራ የተጠቀመበት ሰው ማን ነው?
16. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጡልን ገጸ ባህሪያት መወከል ብትፈልግ የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ግለሰብ መወከል ትፈልጋላችሁ?
17. ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ውስጥ የትኛውን በበለጠ ትወዱታላችሁ? ለምን?
18. በአለም ካሉ አገራት አንድ አገር ሂድ ብትባል የት ለመሄድ ትመርጣለህ?
19. አያድርገውና፤ ቤታችሁ በእሳት እየተቃጠለ ነው እንበል፤ ሁሉም የቤተሰብህን አባላት አስወጥተሃል እንበል ነገርግን እድል አግኝተህ አውጣ ብትባል ካሉህ ንብረቶች ምን ታወጣለህ?
20. የምትወደው ፊልም ወይንም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ምንድን ነው?
21. ከባለፈው ስብሰባችን ጀምሮ በሕይወትህ ላይ ተጽዕኖ ካሳቸው ሰዎች መካከል አንዱ ማን ነው?
22. ባለፈው ሳምንት ከገጠሙህ መልካም ጉዳዮች ምርጡ ምንድን ነው?
23. የገጠማቸውን ተግዳሮት ጥሰው በመውጣት አሁን ያሉበት የደረሱ ሰዎች ውስጥ የአንዱን ስም ጥቀስ፡፡
24. ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት ዋጋ የምትሰጠው አንድ ጉዳይ ምንድን ነው? ከክርስቶስ ጋር ባለህስ ግንኙነት? ከወላጆችህ ጋር ባለህስ ግንኙነት?
25. በቀን ውስጥ የምትወደው ጊዜ የትኛውን ጊዜ ነው?

26. (ሳሳገቡ) ምን አይነት ሰው ነው ማግባት የምትፈልጉት፤ (ሳገቡ) ባለቤታችሁን ለማግባት የመረጣችሁት ለምንድን ነው?
27. (ከድህነት ውጪ) የማትረሳው ስጦታ ምንድን ነው?
28. በሕይወትህ የማትረሳውና በዚህ ሳምንት የከወንከው ምን አይነት ገጠመኝ አለህ?
29. ለሶስት ቀን ብቻ ወደሌላ አገር ሂድ ብትባል የት መሄድ ትፈልጋለህ?
30. አንተ ባለህበት አገር በማንኛውም ዘመን የኖረ አንድን ግለሰብ ለማግኘት ብትችል፤ ማንን ማግኘት ትፈልጋለህ፤ ለምን ይህን ሰው ማግኘት ፈለግህ?
31. በአለም ላይ ካሉ ሃገራት በአንዱ ለመኖር ቢፈቀድልህ የት ለመኖር ትመርጣለህ? ለምን?
32. ምን አይነት (መንፈሳዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አእምሮአዊ ወ.ዘ.ተ...) ስጦታ ለዚህ ቡድን እንዳመጣህ ታምናለህ? (በሌላ አነጋገር የዚህን ቡድን አባላት ሊያበረታታ የሚችል ምን አይነት አስተዋጽዖ ታደርጋለህ?)
33. ለነገሮች የምትሰጠውን ግምት የቀየረ ልምምድህ ምንድን ነው?
34. ለለመጪው አንድ አመት ያለህ እቅድ ምንድን ነው?
35. ወላጆች/አሳዳጊዎችህ እነማን ናቸው፣ ምን ነበር የሚሰሩት፣ ከእነርሱ ስብእና በበለጠ የምታከብረው ምንድን ነው?
36. የሙያ መስክህን እንደገና መምረጥ ብትችል ምን አይነት ሙያ የምትመርጥ ይመስልሃል?
37. በአለም ላይ ካሉ አገራት አንዱን የመምራት እድል ቢሰጥህ የትኛውን አገር መምራት ትፈልጋለህ? ለምን?
38. ባለፈው ሳምንት ያሳለፍከው ምርጥ እና መጥፎ ገጠመኝ ምንድን ነው?
39. ለሁለት ሳምንት ዕረፍት የፈለግከበት አገር ሂድ ብትባል የትኛውን አገር ትመርጣለህ? ለምን?
40. አሁን በሕይወት ካሉ ሰዎች አንድ ሰው ለማግኘት እድል ቢሰጥህ ማንን ማግነት ትፈልጋለህ? ለምን?
41. ለእያንዳንዱ ተሳታፊ አንዳንድ ወረቀት በመስጠት፤ የሚሰሩትን ስራ የሚወክል ስዕል እንዲስሉ ስጣቸው፤ ከዚያም ስለስዕላቹ አብራሩ።

42. ዛሬ በዚህ በመገኘትህ ደስ እንዲልህ ያደረገ ጉዳይ ምንድን ነው?
43. ለምሳሌ አንድ 20 ሚሊዮን ብር ተሰጣችሁ እንበል፤ በዚህ ብር ምን ማድረግ እንደሚፈልጉ ግለጹ፡፡
44. የቁልምጫ ስም አለህ፤ ካለህ ማን ይባላል? ሚስትህን በምንአይነት የቁልምጫ ስም ነው የምትጠራት፤ ልጆችህንስ?
45. በታሪክ ውስጥ በኖርኩ ብለህ የምትመኝበት ዘመን አለህ? ካለ ለምን?
46. አንዴት ነው ይህ ቡድን አንተን የጠቀመህ? መልስህን ለቡድኑ በመስጠት አንዳችሁ ሌላችሁን አመስግኑ፡፡
47. ስለ ቤተሰብህ እግዚአብሔርን የምታመሰግንበት ሶስት ነገር ተናገር፤ በመቀጠልም አንዳንድ ጊዜ በጣም የሚከብድህን ሶስት ነገሮች ለቡድንህ አካፍል፡፡
48. በቤተሰብህ ሕይወት አሁን ቢሆን ደስ የሚልህ አንድ ነገር ምንድን ነው? በቤተክርስቲያንህስ? በጥናት ቡድንህስ? በአለም ሁሉስ?
49. በዚህ ጊዜ በሕይወትህ ካሉ ሰዎች ውስጥ ምርጥ ጓደኛዬ ነው የምትለው ማን ነው?
50. በቅርብ ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ መልስ ያገኘህበት የጸሎት ርዕስ አለ?
51. ስራህ ምንድን ነው? ስራህን የምትወድበት ምክንያት አለህ?
52. ማን ነው በክርስትና ሕይወትህ ላይ ከፍተኛ የሆነ በጎ ተጽዕኖ ያሳደረው? ለምን?
53. ሌሎች ቢያነቡት/ ቢመለከቱት ብለህ የምትመክረው መጽሐፍ/ፊልም ምንድን ነው? ለምን?
54. በሕይወትህ እግዚአብሔር ይደሰትበታል ብለህ የምታስበው ምንድን ነው?
55. በዚህ ሳምንት ከተሰጠህ አበረታች ቃላት ውስጥ በጣም የወደድከው የትኛውን ነው?
56. አንተ በዚህ ሳምንት ለሌሎች የሰጠኸው አበረታች ቃል ምንድን ነው?
57. አሁን የምታመልክበት ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ለምን መረጥክ?
58. በሕይወትህ እስካሁን ለመከወን የምትፈልገው ነገር ምንድን ነው?
59. ስለምን ስታስብ ነው በምስጋና የምትሞላው?
60. በሕይወትህ የማትረሳው አንድ ገጠመኝ ምንድን ነው?

61. በጣም ትርጉም የሚሰጥህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምንድን ነው፤ ለምን ትርጉም ይሰጥሃል?
62. ኢየሱስ ከአንድ ሳምንት በኋላ እንደሚመጣ እርግጠኛ ብትሆን አኗኗርህ ላይ የሚለወጥ ነገር አለ?
63. ከተዋወቅሃቸው ሰዎች ውስጥ በጣም አስገራሚው ሰው ማን ነው?
64. ከበአላት ውስጥ በጣም የምትወደው የቱን ነው?
65. ስላለህ የመንፈሳዊ ልምምድ ለቡድንህ አካፍል።
66. ምን ዘና ያደርግሃል?
67. በጣም የምትወዱት መዝሙር ምንድን ነው?
68. በዚህ ሳምንት የገጠመህ እና ለቡድንህ ማካፈል የምትችለው አንድ ጉዳይ ምንድን ነው?
69. አለመሳካት የሚባል ነገር ባይኖር ምን መስራት ትፈልጋለህ?
70. ሕይወትህን እንደገና መኖር ብትችል ምን ትቀይር ነበር?
71. በመቃብር ሃውልትህ ላይ ምን ቢጻፍ ትመርጣለህ?
72. በሕይወት ታሪክህ ላይ ምን ተብሎ ቢነገርልህ ትመርጣለህ?
73. በጨረቃ ላይ መኖር ብትችል፤ ከዚህ ይዘህ መሄድ የምትፈልገው አንድ ነገር ምንድን ነው?
74. ከዚህ ቀጥሎ ያለው ገጠመኝ የገጠማቸው ሰዎች ብታገኝ ምን ታደርጋለህ (1) የተዘረፈ ሰው ብታገኝ? (2) ውሃ ውስጥ እየሰጠመ ያለ ሰው ብታይ? (3) በእሳት እየተቃጠለ ያለ ቤት ብታይ?
75. ስለወንዶች የማይገባህ አንድ ነገር (ሴት ከሆንሽ) ስለሴቶች
76. ሳምንቱ እንደገና ቢደገም፤ አንድ የምታስተካክለው አንድ ነገር ምንድን ነው?
77. ከቤተክርስቲያንህ ውጪ አባል የሆንክበት አንድ ሌላ የጥናት ቡድን ምንድን ነው፤ ቡድኑ እንዲቀጥል ወይንም እንዳይቀጥል ያደረገው ነገር ምንድን ነው? ስለጥናት ቡድን ስናነሳ ከዚህ የተለየ ወይንም የኃይማኖት ስብስብ ያልሆነም ቡድን ካለ ስለዚያም ማውራት ትችላለህ። ብዙዎቻችን በስራ ቦታችን በትናንሽ ቡድኖች እንሰባሰባለን።

78. አንድ የማትረሳው የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ አለ (ጥምቀት፣ ሰርግ፣ ወደጌታ ስመጣ ወ.ዘ.ተ...)? ይህ ስጦታ ትርጉም ያለው መሆኑን ለቡድንህ አካፍል፡፡
79. ስለእግዚአብሔር ስታስብ ወደሀሳብህ የሚመጣው አንድ ነገር ምንድን ነው?
80. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት ጥያቄ የሚሆንብህ አንድ ነገር ምንድን ነው?

## ለጥናት ቡድኖች የቀረበ የትግበራ ናሙና

ከዚህ በታች የቀረበው በትናንሽ ቡድኖች ጥናት ውስጥ ለሚመጡ አራት የትግበራ ቅደምተከተሎች እንደናሙና የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህ ናሙና ለእያንዳንዱ ትግበራ የተቀመጠው ጊዜ ከትክክለኛው የጊዜ ፍጆታ ጋር የተጠጋጋ ነው፡፡

| ሕብረት | አምልኮ | ማነጻት | ወንጌል ስርጭት |
|---|---|---|---|
| ግለሰብ ከግለሰብ | ሰው ለ እግዚአብሔር | እግዚአብሔር ለ ሰው | የክርስቶስ አካል ለአለም |
| "ወደ ውስጥ" | "ወደ ላይ" | "ወደ ታች" | "ወደ ውጭ" |
| 20 ደቂቃ | 20 ደቂቃ | 30 ደቂቃ | 20 ደቂቃ |
| • የሚያዝናኑ ተግባራትን ከውኑ<br>• አብራችሁ ተመገቡ<br>• አንዳችሁ ሌላችሁን በሚገባ ለማወቅ ሞክሩ<br>• አንዳችሁ ሌላችሁን አበረታቱ<br>• ደስታችሁን ተጋሩ<br>• ችግሮቻችሁንም ተጋሩ<br>• አንዳችሁ ለሌላችሁ ጸልዩ | • የምስጋና መዝሙር ዘምሩ<br>• እግዚአብሔርን ስለ ታላቅነቱ አምልኩት<br>• ለሳደረገላቹ መልካም ነገር ሁሉ አመስግኑት<br>• ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ወይንም በለሆሳስ ጸልዩ<br>• ለአምልኮ የተጻፉ ክፍሎችን ከቃለ እግዚአብሔር አንብቡ (ምሳሌ መዝሙረ ዳዊት)<br>• መንፈሳዊ ግጥሞችን አንብቡ | • እንደ ቡድን ለታጠኑ የመረጣችሁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አጥኑ<br>• በእያንዳዱ ቀን ለሚገጥመን ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህን ተግባራዊ አድርጉ<br>• ከቡድንህ ጋር በአገልግት ተሳተፉ<br>• የጸጋ ስጦታህ ምን እንደሆነ እወቅና ጥቅም ላይ አውል<br>• የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቃልህ ለመያዝ አጥና፡፡ | • ከጸሎት ርዕስ መጻፊያ ደብተራችሁ ለመዘገባችኋቸው ያልዳኑ ሰዎች ካሉ ለእነርሱ ጸልዩ<br>• ያላመኑ ሰዎችን ወደ ቡድን ጥናታችሁ ጋብዙ<br>• የቡድን ጥናት በሚደረግበት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ፍላጎት ለመድረስ ተንቀሳቀሱ<br>• ካላመኑ ሰዎች ጋር "ጓደኞች" ሁኑ<br>• መልካሙን የምስራች ላልሰሙ አሰሙ፡፡ |

# ክፍለ ትምህርት 4

# ከመልዕክቱ አሳብ መውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን

## ዘዴ 2፡- የእግዚአብሔርን ቃል ጥናት ምልከታ (60 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ይህን ክፍለትምህርት የምንጀምረው ከመልእክቱ አሳብ ውሰድ የተሰኘውን የጥናት ዘዴ መለሶ ቀኝት በማድረግ ነው፡፡ የሚከተለውን ጥያቄ ለቡድኑ አቅርብ "ከመልዕክቱ አሳብን መውሰድ የጥናት ዘዴ ውስጥ የሚገኙ ሶስት ተግባራትን እና ከተግባራቱ ጋር ተያይዘው የሚጠየቁ ሶስቱ ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው?" ተሳታፊዎች እንደሚከተለው መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡

1. <u>ምልከታ</u> - ክፍል ምን ይላል?
2. <u>መተርጎም</u> - ምን ማለት ነው?
3. <u>ማዛመድ</u> - ምን ማድረግ ይገባኛል?

እንዲህ በል "በዚህ ክፍለትምህርት ስለ መጀመሪያው ተግባር ማለትም ስለምልከታ እንማራለን"

ምልከታ - የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ክፍሉ ምን ይላል? (20 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ተሳታፊዎች በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ ተገቢውን ቃል እንዲሞሉ ንገራቸው፤ ከዚያም በሚከተሉት ጥያቄዎች ውይይት አድርጉ፡፡

1. ክፍሉ ምን እንደሚል ለማወቅ በጥንቃቄ ለመመልከት <u>ተዘጋጅ</u>፡፡

- የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምንድን ነው? 1ቆሮ 2፡14
- የጸሎት ሚና ምንድን ነው? ኤፌ 1፡18

- ስመታዘዝ ዝግጁ የመሆን ሚና ምንድን ነው? ያዕ 1፡22-25
- በተጠናው ቃስ እግዚአብሔር ብርሃን መሰረት ራስን የመመርመር ሚና ምንድን ነው? 2ቆሮ 13፡5
- ስመማር ፍቃደኛ የመሆን ሚና ምንድን ነው? ሐዋ 17፡11

2. በቂ <u>ጊዜ</u> ውሰድ

- ምን ያህል ጊዜ ነው በቂ የሚሆነው?
- የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና ስማጥናት የተኛው ጊዜ ስእናንተ ምቹ ነው?
- የትስ ነው ያስረብሻ ቃስ እግዚአብሔርን ማጥናት የምትችሉበት ስፍራ?

3. <u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ</u> አውዱን ተመልከት (ሁኔታውን) የሚከተሉትን አመዛዝን፡-

- ከመረጥነው ክፍል ቀደም ብሎ ያለው እና ከክፍሉ ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ስለምን ያወራል?
- ስጥናት የመረጥነው አንቀጽ ጭብጥ ምንድን ነው?
- የምዕራፉ ጭብጥ ምንድን ነው?
- መጽሐፉ የተጻፈበት ዓላማ እና ጭብጥ ምንድን ነው?

4. የጥናት ክፍሉን <u>አደረጃጀት</u> መርምር

- የጥናት ክፍሉ ምን አይነት የስነጽሑፍ ዘውግ ይዟል?
- የጥናት ክፍሉ ቁልፍ ቃል ምንድን ነው?
- ምን አይነት ነገሮች ተወዳድረዋል፤ ምን አይነት ነገሮችስ በንጽጽር ቀርበዋል? ክፍሉን ስታነብብ የክፍሉ አሳብ እንዴት እንደተደራጀ ተመልክተሃል?
- ግሶቹ ምን ምን ናቸው? (ግሶች ድርጊትን ያመስክታሉ)
- አያያዥ ቃላት በክፍሉ ውስጥ የት እና እንዴት ተገለጡ? (እነዚህ ደግሞ ከአንድ አሳብ ወደ ሌላ አሳብ የተደረገን ሽግግር ያመለክታሉ)

- የማመሳከሪያ መግለጫዎች ምንድን ናቸው?

5. <u>የምርመራ</u> ጥያቄዎችን ስክፍት ጠይቅ

ስለ ስአንድ ክስተት የአይን እማኝ የሆነን ሰው ዜና ዘጋቢዎች የሚጠይቁትን አይነት ጥያቄዎች ስክፍት ጠይቅ።

- ማን?
- ምን?
- የት?
- መቼ?
- እንዴት?
- ለምን?

## ከመፅሐፉ ሐሳብ የመውሰድ ጥናትን በተግባር ማሳየት፡-

## ምልከታ (40 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ከላይ በቀረበው የምልከታ መርህ መሰረት ተሳታፊዎች ኤር 1፡4-10 እንዲያጠኑ አድርግ፡፡ ከመጀመርህ በፊት መጸለዩን አትርሳ፤ ከዚያም ምንባቡን ለሁሉም ካነበብክ በኋላ የክፍሉን አውድ እና አደረጃጀት ምን እንደሆነ ተወያዩ፡፡ ከዚያም ተሳታፊዎች ከታች "የምልከታ ናሙና" በሚለው ርዕስ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ለ30 ደቂቃ ተወያዩ፡፡ ከዚያም ያገኛችሁትን ውጤት በተመለከተ ሴላ ውይይት አድርጉ፡፡

የምርመራ ጥያቄዎች፡-

ማን?

- ይህን የጥናት ክፍል የጻፈው ማን ነው (ቁጥር 1) ?
- በክፍሉ የተጠቀሱት ሰዎች ማን ማን ናቸው (ቁጥር 5)?
- በቁጥር 5 ላይ የሚናገረው ማን ነው?
- በዚህ የምንባብ ክፍል አውድ ውስጥ ስማቸው የተገለጠ ሰዎች ማን ማን ናቸው (ቁጥር 1-3)?
- በ "ማን" የሚጀምሩ ሌሎች ጥያቄዎች አሉ…?

ምን?

- በዚህ ክፍል አውድ ውስጥ የተከናወኑ ቁልፍ ተግባራት ምንድን ናቸው?
- ለኤርሚያስ የመጣለት "የእግዚአብሔር ቃል" ምንድን ነው (ቁ. 5)?
- በ ቁ.5 የተገለጠ እግዚአብሔር ሲፈጽመው የተናገረው አራት በግልጥ የተቀመጡ የድርጊት እቅዶች ምንድን ናቸው?
- በቁ.5 የኤርሚያስ ሚና ተደርጎ የተቀመጠው ምንድን ነው?

- በቁ.5 መሰረት የኤርሚያስ ሚና እስከምን ድረስ እንደሆነ ይናገራል? በእስራኤል ብቻ የሚቀር ወይንስ ከዚያ ውጪ ሳሉም ለህዛብ የሚሆን?
- በቁጥር 6 የምንመለከተው የኤርሚያስ ምላሽ ምን ነበር?
- እግዚአብሔርስ ለኤርሚያስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር (ቁ7-8)?
- በቁ 7 እና 8 እግዚአብሔር ለኤርሚያስ የሰጠው ሁለት መመሪያ ምንድን ነው?
- በቁ.7 መሰረት ኤርሚያስ ምን አይነት አማራጭ ነበረው?
- በቁ.8 የመጀመሪያው ክፍል ላይ እግዚአብሔር ለሰጠው ምላሽ የኤርሚያስ ስሜት ምን ይመስል ነበር?
- ኤርሚያስ እንዳይፈራ የተሰጠው ሁለት ምክንያት ምን ነበር (ቁ. 8)?
- በቁ.9 እግዚአብሔር ለኤርሚያስ ያደረገለት አንድ ነገር ምንድን ነው?
- በቁ. 10 ላይ የተዘረዘረው የኤርሚያስ ተግባርና ኃላፊነት ምን ነበር?
- ከዚህ ክፍል ቀጥሎ የሚመጣው ምንባብ ላይ እግዚአብሔር ምን ሲከውን እንመለከታለን (ቁ. 11-16፤ 17-19)?
- ሌሎች "ምን" ጥያቄዎች...?

የት?

- የክፍሉ አውድ የት እንደሆነ ይናገራል (ቁ.1)?
- እነዚህ ስፍራዎች የት ነው የሚገኙት?
- ኤርሚያስ ከእግዚአብሔር ይህን ጥሪ ሲቀበል የት አካባቢ ሊሆን ይችላል (ቁ.1)?
- ሌሎች "የት" ጥያቄዎች...?

ለምን?

- እግዚአብሔር ለምን ኤርሚያስን ጠራው?
- ኤርሚያስ እንዲያነብይ የማገልገሉ ጥቅም ምንድን ነው?

እንዴት?

- ኤርሚያስ በቁ.1 እንዴት ነበር የተገለጠው?
- እዴት ነው የኤርሚያስ አባት ኬልቂያ በቁ.1 ላይ የተገለጠው?
- እንዴት ነው ኤርሚያስ በቁ.6 ለእግዚአብሔር ስለራሱ የገለጠው?
- እንዴት ነበር ኤርሚያስ ከእግዚአብሔር ስለመጣለት ቃል ምላሽ የሰጠው (ቁ.6)?
- እንዴት ነው እግዚአብሔር በቁ.18 ኤርሚያስን የገለጠው?

## ለሞጁል 3 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡-

### ከክፍሉ አሳብ መውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፡- ምልከታ

ኤር 1፡1-10 ያለውን ክፍል ምልከታ በተሰጠው ጊዜ ማጠናቀቅ ካልቻላችሁ የሚቀጥለውን ጥናት ከመጀመራችሁ በፊት ይህን ምልከታ አጠናቀቁ፡፡ በዚህ ክፍል ካነሳናቸው ጥያቄዎች ውስጥ ምንአልባት መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች ካሉ ተሳታፊዎች እንዲያነሱ እድል ስጥ፡፡ ከዚያም እነዚህን ጥያቄዎች በጽሑፍ አስፍረህ አስቀምጥ እና ሌላ ጊዜ ትጠቀምበታለህ፡፡

# ክፍል ትምህርት 5

# ለቤተክርስቲያን አጋዥ የሚሆንን የጸሎት አጋር ማስተባበርና ማንቀሳቀስ (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** ወረቀት ወይንም ካርድ ለተሳታፊዎች በመስጠት በዚያ ላይ ከዚህ በታች የቀረቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዲጽፏ ማድረግ፤ ከዚያም በክፍል ውስጥ መስጠፍ፡፡ በክፍል ውስጥ የተሰጠፉትን ጥቅሶች የሚያነቡ ከየቡድኑ የተመረጡ ሰዎች እነዚህን ጥቅሶች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለቡድኑ ያንብቡ፡፡ ከዚያም ተመልሰው በሌላ ወረቀት ካነበቧቸው የቃለ እግዚአብሔር ምንባቦች ውስጥ ለወንጌል ስርጭት ጸሎት ወሳኝ እንደሆነ የሚያካትቱትን ጥቅሶች ይጻፉ፡፡ ይህን ተግባር ለመፈጸም 5 ደቂቃ ስጥ፡፡ ከዚያም የጻፉትን እንዲያነቡ እና ለቡድናቸው እንዲያካፍሉ አንድ ደቂቃ ስጡ፡፡

**ጸሎት፡ የቤተክርስቲያን ተከላና ወንጌል ስርጭት አገልግሎት አስፈላጊ ግብአት**(10 ደቂቃ)

ከዚህ በታች ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንበብ ጸሎት ለወንጌል ስርጭት እና ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚጫወተውን ሚና አብራሩ፡፡

ሮሜ 10፡1

ኤፌ 6፡18

ኤፌ 6፡19-20

ቆላ 4፡2-4

2ተሰ 3፡1-3

እንዴት ነው ጸሎትን ከወንጌል ስርጭት ጋር ማዋሃድ የሚቻለው? (5 ደቂቃ)

እንዲህ በል "ምን አይነት ተግባራት ሰዎች ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል?"

1. <u>በቡድን ጥናት</u> ውስጥ

2. ለሶስት ሆኖ መጸለይ - ሶስት አማኞች አብረው ሲጸልዩ።

3. <u>የጉዞ ጸሎት</u> - ቤተክርስቲያኒቱን ለመትከል ባሰባችሁት ስፍራ እየዞራችሁ ጸልዩ፤ እንደየ አስፈላጊነቱ ወሳኝ የምትሏቸው ስፍራዎች ጥቂት ጊዜ ቆማችሁ በውስጣችሁ (ያለድምጽ) ጸልዩ።

## የጉዞ ጸሎትን የተመለከተ ውይይት (15 ደቂቃ)

የአሰልጣኙ መምሪያ፡- ከዚህ በታች የሰፈረትን ሁለት ትርክቶች ካነበባችሁ በኋላ፤ ከትርክቱ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው።

**የገጠመኝ/ታሪክ ጥናት 1፡-**

አንድ በጣም በብዙ ችግር የተተበተቡ ቤተሰቦች ያሉበት አካባቢ ለቤተክርስቲያን ተመረጠ። በዚህ አካባቢ የሚከተሉት ማህበራዊ ችግሮች የነበረበት፤ ስራ አጥነት፣ የቤተሰብ መበተን፣ የዕጽ ሱሰኝነት እና ወንጀል፤ እነዚህ ማህበራዊ ቀውሶች የተለመዱ ናቸው። ቤተክርስቲያኒቱን ከመተከሏ በፊት የጉዞ ጸሎት በእያንዳንዱ መንግድ እንዲደረግ እቅድ ተያዘ። ታዲያ ይህን የጉዞ ጸሎት በሚደረግበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ወደ ልባቸው የሚያመጣውን መዝግበው ያኖሩ ነበር። እንደመጀመሪያው ያሉ ብዙ የጉዞ ጸሎቶች ተደረጉ። ጸሎቶቹ የተደረጉት በትምህርት ቤቶች አካባቢ፣ በገበያ ስፍራዎች እና ከአካባቢው ዳርቻዎች(በሰፈረ ዙሪያ) ነበር የተደረገው። ሌላው ይህ የጉዞ ጸሎት ያካተተው ስፍራ ደግሞ ዕጽ የሚዘዋወርባቸውና ጥንቀሳ የሚያካሂዱ ሰዎች ምልክታቸውን የሚሰቅሉባቸው ጫካዎችንም ጭምር ነበር። ጸሎቱ እንዲህ ያሉ የአጋንንት

አሰራርን እና ተጽዕኖንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለማፍረስ ይደረግ ነበር፡፡ ጸሎቱ በተጀመረ ሶስተኛው አመት በዚህ አካባቢ ያለ የማህበረሰብ ቀውስ መገለጫ የሆነው ወንጀል በ40% ቀንሷል፤ ከ70-80 አባላት ያሉት ቤተክርስቲያን ተተክሏል፡፡ ከዚህም የተነሳ የቅድስና አየር በአካባቢው መንፈስ ጀምሯል" እግዚአብሔርም በብዙዎች ሕይወት ውስጥ እየሰራ ይገኛል፡፡

- ይህን ትርክት በተመለከተ ምን አይነት አስተያየት መስጠት ትፈልጋለህ?
- እንዲህ ካለው የጉዞ ጸሎት ምን አይነት ውጤት ይገኛል?
- ምንድን ነው ትልቁ ተግዳሮት?

**የገጠመኝ/ታሪክ ጥናት 2፡-**

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ እና ባለቤቱ ቤተክርስቲያን ተተክሎ ማየት ወደሚፈልጉበት ከተማ ወደ ሚገኝ አንድ የጋራ መኖሪያ ህንጻ ኑሯቸውን ለማድረግ ገቡ፡፡ አንድ ቀን ምሽት ላይ እኚህ ባልና ሚስት በህንጻው ውስጥ እየተንቀሳቀሱ፤ ቆየት ብለው ደግሞ ከጋራ መኖሪያው መግቢያ ፊትለፊት ቆመው በዚያ ለሚንቀሳቀሰው ሰው ሁሉ ይጸልያሉ፡፡ አንዱ ልጃቸው ይጸልይ የነበረው እያንዳንዱ በዚያ የሚኖር ሰው ኢየሱስ ለሕይወቱ አንደሚያስፈልገው እንዲያምን እና እንዲጠይቅ ነበር፡፡ ሴላኛዋ ልጃቸው ደግሞ እያንዳንዱ ነዋሪ የሚያስፈልገው የገንዘብ ፍላጎት እንዲሞላ ስትጸልይ፤ ሴላኛዋ ልጃቸው ደግሞ መልካም የሆነ የቤተሰብ ግንኙነት በእነዚህ ነዋሪዎች ሕይወት እንዲኖር ትጸልይ ነበር፡፡ እናታቸው በዚያ የጋራ መኖሪያ ለሚኖሩ ሰዎች ጤና ስትጸልይ፤ አባታቸው ደግሞ የእግዚአብሔር በረከት በእያንዳነዱ ቤተሰብ ላይ እንዲሆን ይጸልይ ነበር፡፡ ይህን የጉዞ ጸሎት ከጸለዩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ 14 ሰዎች ጌታን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ በዚህም ቤተክርስቲያን ለመትከል በቁ፡፡

- ይህን ትርክት በተመለከተ ምን አይነት አስተያየት መስጠት ትፈልጋለህ?
- እንዲህ ካለው የጉዞ ጸሎት ምን አይነት ውጤት ይገኛል?
- ትልቁ ተግዳሮትስ ምንድን ነው?

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-** "የጸሎት ቡድንን ማቋቋም" እና "ለጸሎት የሚሆን መረጃን መሰብሰብ" ለሚሉት አርዕስት እነዚህን ለማብራራት ከዚህ በታች የተቀመጠውን ጥያቄ በማንሳት ተሳታፊዎች ሁሉ እንዲወያዩ አድርግ (20 ደቂቃ)፡፡

**የጸሎት ቡድን ማቋቋም**

- ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህ በቡድን የሚጸልዩልህ ሰዎች አሉ? እንዴት ነው ይህ ጸሎት እየረዳህ ያለው? የጸሎት ቡድኑ በምን ዙሪያ እንዲጸልዩልህ ነው የጠየቅኸው?
- በምን አይነት መንገድ ነው ለጸሎት ቡድኑ የጸሎት ርዕስህን እና የተመለሰልህን መልስ እንዳገኘህ የምታስታውቀው?
- ምን አይነት መረጃዎች ናቸው ከጸሎት ቡድኑ ጋር ብትወያይባቸው መልካ የሚሆኑት እና ምን አዩነት መረጃዎችስ በግል መያዝ አለባቸው?
- ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህ የሚጸልዩ ሰዎችን ቁጥር እንዴት ማብዛት ይቻላል?

**ለጸሎት የሚሆን መረጃን መሰብሰብ**

- ምን አይነት መረጃዎችን ለግለሰብ ወይንም ለማህበረሰብ በጥናትና ምርምር ሂደት እናገኛለን ደግሞስ እንዴት ይህን መረጃ ለጸሎት እንጠቀምበታለን?
- በአካባቢው ስለሚገኙ ቤተክርስቲያናት፣ የባእድ አምልኮ ስፍራዎች፣ የቤተክርስቲያን እድገት እና የአማኞች ህብረትን የተመለከተ መረጃ አንዴት ለጸሎት ሊጠቅም ይችላል? ለምን እንደሚጠቅም አብራራ፡፡

## ለሞጁል 3 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡-

## የጸሎት ቡድን ማቋቋም እና የጉዞ ጸሎት ልምምድ

1. እስካሁን የጸሎት ቡድን ካላቋቋምክ ከወዲሁ መጀመር አስፈላጊ ነው፡፡ ቢያንስ ሶስት ሰዎች ስለ አገልግሎትህ በሳምንት ለአንድ ቀን የሚፀልዩልህን አደራጅ፡፡

እንዴት አድረገህ ነው የምታደራጃቸውን የጸሎት ቡድን ስለ አገልግሎትህ የጸሎት ርዕስ እና የተመለሰልህን መልስ ልታሳውቃቸው ያሰብከው?

2. ቢያንስ አንድ የጉዞ ጸሎት ከጸሎት ቡድንህ አሊያም በመረጥከው ስፍራ ቤተክርስቲያን ተተክሎ ሰዎች ወደ ጌታ ሲመጡ ማየት ከሚፈልጉ ወገኖች ጋር አድርግ፡፡ ይህን ልምምድህን ከማማከርና ድጋፍ አገልጋይህ ወይንም ከአሰልጣኝህ ጋር ተወያይ፡፡

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡- (10 ደቂቃ)**

- የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮችን በዚህ ስልጠና ስላሳዩት ትጋት እና ስለፈጸሙት በጎ ተግባር አመስግናቸው፡፡
- ስለ ጸሎት ኮንሰርት በማስተዋወቅ ይህን ክፍለ ትምህርት አጠናቅቅ፡፡ ቀጣዩን ክፍለትምህርት ማለትም የጸሎት ኮንሰርት የሚለውን ትምህርት ከመጀመራችሁ በፊት ጥቂት ረፍት አድርጉ፡፡

# የጸሎት ኮንሰርት፡ በመዝሙር 95 መሰረት

# ኑ፥ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ በእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ (60 ደቂቃ)

**የአሰልጣኙ መምሪያ፡-**

- ይህ የጸሎት ኮንሰርት ተሳታፊዎችን የምታስተምርበት ሳይሆን፤ በህብረት የምትጸልዩበትን ጊዜ የምትወስዱበት፤ እንደመሪ የጸሎት ህብረቱን የምትመራበት ጊዜ ነው፡፡ ይህን ክፍለትምህርት ከመጀመርህ በፊት መዝሙር 95ን በሚገባ ማጥናት እና አከፋፈሉን መገንዘብ ይገባሃል (ገለጻውን ለማግኘት በዚህ ክፍለትምህርት ማብቂያ ላይ ያለውን ክፍል ተመልከት)፡፡
- ይህ የጸሎትና አምልኮ ጊዜ እያንዳንዱ በዚህ ስልጠና የሚሳተፍ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የትምህርቱን ይዘት እንዲረዳ እና በሕይወቱና በአገልግሎቱ ውስጥ የሚገባውን ጉዳይ በትህትና እግዚአብሔርን በመጠየቅ ምሪት እንዲቀበል የሚያግዝ መሆን አለበት፡፡
- ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ በመጠቀም የምታዘጋጀውን የጸሎት ኮንሰርት እንዴት እንደምታቅድ፣ እንደምትዘጋጅ እና እንደምትተገብር ግንዛቤ ታገኛለህ፡፡
- የተለያዩ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮችን በመጠቀም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ በዝማሬ እግዚአብሔርን እንድታመልኩ የሚዘምር፣ ጸሎቱን የሚመራ እና ምስክርነት የሚሰጥ በማድረግ ፕሮግራሙን አደራጅ፡፡
- ከላይ ለጠቀስካቸውና በፀሎት ኮንሰርት ውስጥ ለሚካተቱ ፕሮግራሞች ለእያንዳንዳቸው 20 ደቂቃ መድብ፡፡

**የጸሎት ኮንሰርት ምንድን ነው?**

"የጸሎት ኮንሰርት" የሚለው ቃል የመጣው በ1700ዎቹ ጀምሮ ባሉ ትውልዶች ባለ ክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረግን ወሳኝ የጸሎት መነቃቃት እና በአለም ላይ የክርስቶስን መንግስት ለማስፋት ከዚህ ጸሎት በኋላ የሚመጣን ውጤት የሚጠቁሙ ተግባራትን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ በ*The Eager Feet,*በተሰኘ እና በ ዶ/ር J. Edwin Orr በተጻፈ መጽሐፍ እንዲህ ተዘግቦልናል "በታላቋ ብሪታኒያ በ1780ዎቹ እና በአሜሪካ በ1790ዎቹ በአሜሪካ የነበረው የጸሎት መነቃቃት እና በተጨማሪ በሁለቱም አገራት እንደገና የተገለጠው የተሃድሶ የጸሎት ኮንሰርት...ጥርት ባለ ሁኔታ የሚያሳየን በእነዚህ አገራት ያሉ ቤተክርስቲያናት በአለም ላይ በግልጥ የሚታይ መነቃቃት ያመጡትን የወንጌል ተልዕኮ አገልግሎት ለማስጀመር አማኞችን ለማስታጠቅ እና ለማሰማራት በአገር ደረጃም "ዋተር ሉ" በተሰኘው የጦርነት አውድማ አሸናፊነትን ያቀዳጃቸውን ወታደራዊ ኃያልነት ያገኙት ከዚሁ ከጸሎት ኮንሰርት ነው፡፡ የዚህ ዘመን የመጀመሪያ አካፋይ (የ1800ዎቹ)፣ እያንዳንዱ የወንጌል ተልዕኮ (1858 ወደዚህ ያለው) አገልግሎት በተጨባጭ ከእነዚህ በጸሎት ኮንሰርት መነቃቃት ካገኙ አብያተ-ክርስቲያናት የተገኙ ናቸው፡፡"

እንደታሪክም ካነሳነው፤ የጸሎት ኮንሰርት ሁለት መሰረታዊ አጀንዳዎችን ታሳቢ አድርጎ የተጀመረ ነው 1) ክርስቲያን ወገኖች የክርስቶስ ፍጹም ሙላት፣ ሙላቱ በሆነችው በራሱ ቤተክርስቲያን ተገልጦ በፊታቸው ያለውን የወንጌል አደራ የሚወጡበት አቅም እንዲኖራቸው 2) ሌላኛው አጀንዳ ደግሞ የእርሱ የማዳን ኃይል በእነዚህ በተነቃቁ እና ራሳቸውን በሰጡ ቤተክርስቲያናት ህዝቦች ሁሉ እንዲፈጸም ነው፡፡ ዛሬም እንዲሁ ይኸው ድርብ አጀንዳ ይገለጣል፡፡

ለዚህም ነው "የጸሎት ኮንሰርት" ክርስቲያኖች ያለማቋረጥ ሙላትን እና ክንውንን ያገኙ ዘንድ የሚያደርጉት የጸሎት ህብረት ነው የምንለው፡፡ ከመታወቅ በላይ የሆነ የህብረት ጸሎት በጸሎቱ ርዝመት ወይንም በምን ያህል የጊዜ ርቀት ተደረገ የሚለውን የሚያሳይ ሳይሆን ምን ያህል በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን የእርሱን መሻት "እንደ ኮንሰርት/በህብረትና በደስታ" ጸልየዋል የሚለውን የሚያሳይ ነው፡፡

ዛሬ የሚኖረን "የጸሎት ኮንሰርት" በመዝሙር 95 መሰረት ነው። ይህ መዝሙር በሶስት ደረጃ በተከፈለ ሂደት ጸሎታችንን ይመራል። እነዚህም ደረጃዎች ከዚህ በታች ተቀምጠውልናል።

| መዝሙር 95 | |
|---|---|
| 1. ለእግዚአብሔር ዘምሩ | ቁ. 1-5 |
| 2. ለእግዚአብሔር ስገዱ | ቁ. 6-7 |
| 3. እግዚአብሔርን እንስማ | ቁ. 8-11 |

## ኑ፥ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ በእርሱ ባደረገን

## በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ

## በመዝሙር 95 መሰረት

1. እግዚአብሔርን አክብሩ፡ መዝ 95፡ 1-5ን አንብቡ

ኑ ለእግዚአብሔር በደስታ እንዘምር

- የደስታ መዝሙር **ዘምሩ**
- ለደህንነታችን አለት ለሆነው ለኢየሱስ በፊቱ ድምጻችሁን አንስታችሁ **እልል በሉ/ጩኹ**
- የማዳን ኃይልን የሚናገረውን ክፍል ከመዝ 18፡1-3፣ 30-36 ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ **በህብረት አንብቡ**።
- በእግዚአብሔር ፊት በምስጋና **ቅረቡ**
- **የምስክርነት ጊዜ ይኑራችሁ**፤ በዚህ ጊዜ በተለይ እግዚአብሔር ለሶስት ሆናችሁ በጸለያችሁበት እና ሌሎች ጸሎቶችንም ስለ ቤተክርስቲያን ተከላ ጸልያችሁ የሰማችሁትን እና የመለሰላችሁን በማንሳትና እንዴት ለዚህ መልስ እንደሆነላችሁ በመንገር አመስግኑ።
- እግዚአብሔርን በሙዚቃ እና ዝማሬ **ከፍ አድርጉት**፤ ከመጀመሪያው መዝሙር በኋላ ይህ የተለየ የዝማሬና ጌታን ከፍ የምናደርግበት ጊዜ መኖሩ አስፈላጊ ነው።
- መዝ 95፡3-5 ያለውን **በጋራ አንብቡት**፤ በመላው አለም ላይ ለላለው ሉአላዊ አገዛዙ **አመስግኑት**።

2. ጌታን አምልኩ፡- መዝ 95፡6-7 ያለውን ክፍል አንብቡ

- በሰፊን በእግዚአብሔር ፊት እንስገድ…እንበርከክ (የአካል እንቅስቃሴህ በክፍሉ የተገለጠውን አሳብ እንዲያንጸባርቅ እና የመዝሙሩን መልዕክት እንደያገላ በፈቃድህ ተግብረው፡፡)
- ተሳታፊዎች በመገዛት መንፈስ እንዲጸልዩ አበረታታቸው፤ እናም የሚችሉ ከሆነ ተንበርክካችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡
- እርሱ አምላካችን ነው…እኛም የማሰማርያው በጎች የእጁም ስራ ነንና፡፡
- በግል የሕይወትህ ጠባቂ እረኛ እንደሆነ እውቅና ስጥ፡፡ ስለጥበቃውና እንክብካቤው አመስግነው፡፡
- ሲናገር ትሰማው ዘንድ ልብህን የተመቸ እንዲያደርገው እርሱን ለምን፡፡

3. ድምጹን ስሙ ልባችሁንም አታጽኑ (አታጠንክሩ)፡- መዝ 95፡8-11

- የምታውቁት ኃጢአት በሕይወታችሁ ካለ ተናዘዙ፤ 1ዮሐ 1፡9ን አንብቡ፡፡
- ጌታን ለመስማት ጊዜ ውሰድ፤ በተማራችሁት መሰረት ትክክለኛ ፍሬ እንዳታፈሩ እንቅፋት የሚሆኑባችሁ አሮጌ አስተሳሰብ፣ ልምምድ ወይንም ለአሁን ዘመን ትርጉም የሌለውና ተገቢ ያልሆነ የቤተክርስቲያን ተከላ ስለት ካለ እግዚአብሔር እንዲያሳያችሁ ጸልዩ፡፡ ልትይዙት የሚገባ እና በሕይወታችሁ እና በአገልግሎታችሁ መለወጥ የሚገባውን ማንኛውም ነገር ይለወጥ እንዲሆን ማግኘት የሚገባችሁን ታገኙ ዘንድ ከእግዚአብሔር ጋር ትግላችሁን ቀጥሉ፡፡
- ዕብ 3፡7-19 ያለውን ክፍል አንብቡ፤ ቁጥር 13 በእያንዳንዱ ቀን እርስ በእርሳችሁ ተመካከሩ ይላል፡፡ ጠቅላላውን ተሳታፊ ሁለት ሁለት ወይንም ሶስት ሶስት በማድረግ አንዳቸው ለሌላቸው የማበረታታት ጸሎት እንዲጸልዩ አድርግ፡፡
- በዝማሬ እና በጸሎት እግዚአብሔርን በመባረክ፤ ከዚያም በዚህ ስልጠና ለተካፈሉ ሰዎች ቡራኬ በመስጠት ክፍለትምህርቱን መዝጋት፡፡

## ቀጣዩ ምንድን ነው?

የአሰልጣኙ መምሪያ፡-

- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በገባቸው መጠን መመለስ የሚፈልጉ ፈቃደኛ ሰልጣኞች ካሉ እድል ስጥ፡-
    1. ቤተክርስቲያን ለመትከል የሚሰጡ ሶስቱ ስነመለኮታዊ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
    2. መንፈሳዊ ካርታ ምንድን ነው፤ ለምንስ ነው አስፈላጊ የሆነው?
    3. አራቱ የትናንሽ ቡድኖች ተግባራት ምን ምን ናቸው፤ ቅደም ተከተላቸውስ?

4. ከመጽሐፉ መልእክት በመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ ውስጥ ምልከታ ስናደርግ ምንድን ነው የምንመለከተው?
5. ስቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎትህን ስመደገፍ የጸሎት ህብረት ማቋቋም የምትችልበት ተግባር ምንድን ነው?

- ተሳታፊዎችን እንደ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች በዚህ ስልጠና ያስደመማቸው፣ ያበረታታቸው ወይንም ያነቃቃቸው በዚህ ስልጠና የተማሩት እውነት ካለ እንዲናገሩ እድል ስጣቸው፡፡
- ስሞጁል 3 የተዘጋጀውን የትግበራ እንቅስቃሴን ከቃኛችሁ በኋላ ከዚህ ትግበራ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡
- ተሳታፊዎች ስዚህ ወር የሚሆን ግብ እንዲያስቀምጡ አበረታታ፡፡

ወደ ሚቀጥለው ሞጁል ከማለፋችሁ በፊት የሚከተሉትን ተግባራት እንድትከውኑ እናበረታታችኋለን፡-

- 10 ከዚህ በፊት የማታውቋቸውን ሰዎች ተዋወቁ፡፡
- ስአምስት ሰዎች ወንጌል ስበኩ
- አንድ አዲስ የጥናት ቡድን መስርቱ

ስሞጁል 3 የሚሆን የትግበራ እቅድ፡ የመከታተያ ቅጽ

- የመንፈሳዊ ካርታ ተግባራን አጠናቅቁ (ክፍል ትምህርትን 1ን ተመልከቱ)
- ምስክርነትህን አደራጅተህ አማኝ ሳስሆኑ 5 ሰዎች አካፍል (ክፍስ ትምህርት 2ን ተመልከት)
- ከመልእክቱ አሳብ የመውሰድ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴን በመጠቀም በኤርሚያስ 1፡4-10 ላይ የጀመርከውን ጥናት በመጁል ሶስት ትምህርት ወቅት ማጠናቀቅ ትችላለህ (ክፍልትምህርት 4ን ተመልከት)
- የጸሎት ድጋፍ የሚየደርጉልህን ሰዎች በጉዞ ጸሎት እንዲተባበሩህ አድርግ (ክፍስትምህርት 5ን ተመልከት)፡፡

| ለዚህ ወር የሚሆን የቤተክርስቲያን ተከላ ግብ | |
|---|---|
| **ግለሰቦች** | |
| የተዋወቅናቸው ሰዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| ወደጌታ በቅርብ የመጡ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በቅርብ የውሃ ጥምቀት የወሰዱ | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በስልጠና ላይ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| **ትናንሽ ቡድኖች** | |
| አዳዲስ ትናንሽ ቡድኖች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ የሚሳተፉ አባላት | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |
| በጥናት ቡድኖች ውስጥ ያሉ መሪዎች | እባክዎን በቁጥር ያስቀምጡ |